# ድሬ

19ኛ ዓመት ቁጥር 864 ሳምንታዊ ዕትም

ረቡዕ

የካቲት / 20 / 2016 ዓ.ም



ይፍጠኑ!

እስከ የካቲት 30/2016 ዓ.ም ድረስ ብቻ የሚቆየውን የማህበረሰብ አቀፍ ጤና መድን የአባላት ምዝገባና ዕድሳት ያከናዉኑ።

የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ይሁኑ!

የድሬዳዋ አስተዳደር ጤና ቢሮ


## ታሪካዊው የድሬዳዋ ምድር ባቡር የመንገደኞች ተርሚናል በ 13.5 ሚሊየን ብር ጥገና ሊደረግለት እንደሆነ ተገለፀ

የድሬዳዋ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ፅ/ቤት ከኢትዮጲያ ቅርስ ባለስልጣን መ/ቤት ባገኘው የገንዘብ ድጋፍ ታሪካዊውን የድሬዳዋ ምድር ባቡር የመንገደኞች ተርሚናልን ለመጠገን የውል ስምምነት የፊርማ ስነ-ስርዓት አከናወነ፡፡




በፊርማ ስነ-ስርአቱ ላይ በመገኘት ንግግር ያደረጉት የድሬዳዋ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሀላፊ የሆኑት አቶ ሚካኤል እንዳለ የድሬዳዋ ምድር ባቡር ረጅም እድሜ ያስቆጠረ በመሆኑና የድሬዳዋን ታሪክ የያዘ በመሆኑ ለከተማችን ከፍተኛ አስተዋፆ እንዳለው አንስተው፤ ይህንን ታሪካዊ ቅርስ ከነሙሉ ገፅታው ለትውልድ ማሸጋገር አስፈላጊ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በዚህም ከኢትዮጲያ ቅርስ ባለስልጣን መ/ቤት ጋር በመተባበር ጥናቶች እንደተደረገና ጥገና ለማድረግ ውሉ እንዳስፈለገ ተናግረዋል ለዚህም ባለስልጣኑን አመስግነዋል፡፡

የኢትዮጲያ ቅርስ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር የሆኑት ወ/ሮ ህይወት ህይሉ በበኩላቸው የድሬዳዋ ምድር ባቡር ተርሚናል በትራንስፖርት ቱሪዝም ውስጥ በርካታ ታሪክ ያለው ግንባር ቀደም ተቋም መሆኑን ገልፀው፤ ይህንን ታሪክ ጠብቆ ለማቆየት ጥገና ማድረግ ተገቢ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የኢትዮጲያ ቅርስ ባለስልጣን ቅርፆችን፣ የመጠበቅ የመንከባከብና የመጠገን ሀላፊነት ያለበት በመሆኑ የድሬዳዋ ምድር ባቡር የመንገደኞች ተርሚናል ላይ የረጅም ጊዜ ጥናት በማከናወን ያሉትን ችግሮች በመለየት እድሳት የሚያስፈልግበትን ቦታ በመለየት ለመጠገን መፈራረማቸውንና በዚህም ስራው በ9 ወራት ይጠናቀቃል ተብሎ እንደሚጠበቅና 13.5 ሚሊየን ብር እንደሚፈጅም ወ/ሮ ህይወት ጨምረው ተናግረዋል፡፡

ስራውም በጥራትና የቅርስ ይዘቱን በጠበቀ መልኩ እንደሚሰራ ያነሱት ዳይሬክተሯ ከተለያዩ የአለም ሀገራት የተውጣጡ የድሬዳዋ አስተዳደር ልጆች ፣ ወዳጆች እንዲሁም ከፈረንሳይ ፣ ከጅቡቲ፣ ከኒጀር፣ ከማሊና ከዩኤስኤን ጨምሮ ከሌሎች የዓለም ሀገራትም የመጡ የዲያሎግ ሂዩማኒቲ አባላት እና ተሳታፊዎች በዚህ ፊርማ ስነስርአት ላይ በመገኘታቸው መደሰታቸውን ገልፀው፤ ተቋሙ ላይ የራሳችሁን አሻራ አሳርፉ ሲሉም መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

ከፊርማው ስነስርዓት በመቀጠልም ከተለያዩ የአለም ሀገራት የተውጣጡ የድሬዳዋ አስተዳደር ልጆች ፣ ወዳጆች እንዲሁም ከፈረንሳይ ፣ ከጅቡቲ፣ ከኒጀር፣ ከማሊና ከዩኤስኤን ጨምሮ ከሌሎች የዓለም ሀገራትም የመጡ የዲያሎግ ሂዩማኒቲ አባላት እና ተሳታፊዎች የባቡር ሸርሸር አከናውነዋል በዚህም ከፍተኛ ደስታ እንደተሰማቸው ገልፀዋል፡፡

**በኤደን ሳሙኤል**

**ፎቶ፤- ሙሉዓለም ደሴ**

## በጥንታዊቷ ሀርላ ከተማ ከ 6 ተኛ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ረጅም እድሜ ያስቆጠረ ኪነ-ህንጻ በአርኪዮሎጂስቶች ቁፋሮ ተገኘ



ጥንታዊ የሀርላ መንደር የተገነባው በሁለት ዋና ዋና ኮረብታዎች እና ትንንሽ ኮረብታዎች ፣ እንዲሁም ወደ ሰሜን አቅጣጫ ተዳፋት ቦታ ላይ በትልልቅ ድንጋዮች በተካቡ ስፍራዎች ላይ ሲሆን በዚህ መንደር ላይም በርካታ የአርኪዮሎጂካል ቁፋሪዎች በተለይም በመኖሪያ ቤቶች ፣ በመቃብር ስፍራዎች እና መስጊዶች ላይ የተለያዩ ጥናቶችን አድርገዋል።

በፕሮፌሰር ቲሞቲ አሌክሳንደር የሚመራው የሀርላ የአርኪዮሎጂስት ጥናት ቡድን በሀርላ የተለያዩ ጥናትና ምርምሮችን እያደረጉ ሲሆን ጥናቶቹም መስጊዶች ፣ የጌጣጌጥ መስሪያ ህንጻዎች ፣ መቃብሮች ፣ ከኢንዱስትርያል አገልግሎቶች ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ቤቶች ( ምናልባትም የልብስ ፋብሪካ ሊሆን የሚችል) ፣ ሰፋ ያለ የኪነ-ህንጻ አካል ምናልባትም የሲቪል አገልግሎት የነበረው ፣ በርካታ መኖሪያ ቤቶች ፣ መስሪያ ቤቶች ምናልባትም አልባሳት መስሪያዎች እና የመሳሰሉት ጥንታዊ ቅርሶች በአርኪዮሎጂካል ቁፋሪዎች መገኘታቸውን የጥናት ቡድን መሪ ፕሮፌሰር ቲሞቲ አሌክሳንደር ገልፀዋል።

ፕሮፌሰሩ አክለውም ይህን ከ 1400 ዓመት በላይ እድሜ ያለውን የሀገር ሀብትን እስከዛሬ ድረስ በራሳቸው ተነሳሽነት ጠብቀው ለዚህ ያቆዩትን የሀርላ መንደር ህዝብን አመስግነው ወደፊትም እንዲህ አይነት የቅርስ ሀብቶችን ካገኙ ምንም ነገር ሳይነኩትና ሳይቆፍሩት ወደ አጥኚ ቡድኑ ቢጠቁሙ የተሻለ መሆኑንም ነው ፕሮፌሰሩ ያስታወቁት ።

የቅድመ ዘመን ታሪክ ባለቤት የሆነችው ድሬዳዋ ላይ የመካከለኛ ዘመን ታሪክ በሆነው ሀርላ ላይ የተለያዩ ጥናት እና ምርምሮች ተደርገው በርካታ ታሪካዊ ቅርሶች መገኘታቸውን የድሬዳዋ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሀላፊ የሆኑት አቶ ሚካኤል እንዳለ ተናግረው እነዚህን የተለያዩ ተግባራት ይከናወንባቸው የነበሩ ጥንታዊ ቦታዎችን እና በቁፋሮ የተገኙ ጥንታዊ መስጊዶች ለጎብኝዎች በሚያመች ሁኔታ የተዘጋጁ ስለሆኑ በስፍራው በመሄድ መጎብኘት እንደሚቻልም አቶ ሚካኤል


ወደ ገጽ 4 ዞሯል


## አስተዳደሩ በከተማዋ የሚስተዋለውን የቤት ችግር ለመቅረፍ አዳዲስ አሰራሮችን በማምጣት እየሰራ መሆኑን ገለፀ



የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት በመስተዳደሩ በአነስተኛ የቀበሌ ቦታ ላይ የጋራ መኖሪያ ቤት መገንባት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ከአዲስ አበባና ከአዳማ ከተሞች የተገኙ ምርጥ ተሞክሮን ለከተማ ወረዳዎች፣ ለገጠር ክላስተሮች እንዲሁም ለተለያዩ ተቋማት አመራሮችና ለህዝብ ተወካዮች በማቅረብ የውይይት መድረክ አከናውኗል።

መድረኩን በንግግር የከፈቱት የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ገበየሁ ጥላሁን በመስተዳደሩ የሚስተዋለውን የቤት ችግር ለመቅረፍ አዳዲስ አሰራሮችን ከሌሎች ከተሞች በተሞክሮነት በመውሰድ ከሚለከታቸው አካላት ጋር በርብርብ እየሰራ መሆኑን ገልፀዋል።

በዚህም የነዋሪዎችን የቤት ፍላጎትና ተደራሽነትን ለማጣጣምና ችግሩን ለመቅረፍ ከአዲስ አበባና ከአዳማ ከተሞች ምርጥ ተሞክሮ እንደተወሰደና፤ ተሞክሮውንም


ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የድሬዳዋ አስተዳደር የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የ2016ዓ.ም የስድስት ወር የስራ አፈፃፀም እና የቀጣይ ስድስት ወራት እቅድ ከባለድርሻ አካላት ጋር የምክክር መድረክ አካሄዷል



በእቅድ ግምገማ መድረኩ የተቋሙ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ግርማ ተሰማ እንደተናገሩት ተቋሙ በዋንኛነት ሊወጣ ከሚጠበቅበት ተልዕኮ አንፃር ለአስተዳደሩ ለልማት ስራዎች የሚያስፈልጉ ሀብት ማመንጨት፣ሀብትን ማስተዳደር እና የክትትልና ድጋፍ ስራን መስራት ዋንኞቹ እንደሆኑ ተናግረዋል።

ምክትል ቢሮ ኃላፊ ከዚህም ጋር አያይዘው ስራዎቹም በእቅድ የተመሩ እንዲሆኑ ከማድረግ አንፃር የሚገዙ ሀብቶች በመንግስት የግዥ ስርአት እንዲገዙ ማድረግ፣የአንድ እቅድ አንድ ሪፖርት ስርአት ከባለፈው አመት ጀምሮ በዘመናዊ በለማ ሶፍት ዌር ከእጅ ንኪኪ ነፃ በሆነ አግባብ ስራዎች እንዲሰሩ መደረጉ፣የንብረት አስተዳደር ስርአትን ለማዘመን ባለፈው አመት የተጀመረውን ስራ አጠናክሮ ለማስኬድ ለማዘመን ቀሪ ስራዎችን መስራቱን፣በባለፉት ስድስት ወራት ገቢን ከማስተዳደርና የፋይናንስ አስተዳደር ስርአቱ ውጤታማ እንዲሆን ከማድረግ አንፃር በርካታ አበረታች ስራዎች መሰራታቸውን ጠቁመው፤ ቀሪ ስራዎችም ከመድረኩ ከሚገኘው ግብአት በቀጣይ ስድስት ወራት የተሻለ አፈፃፀም እንዲኖር ያደርጋል ብለዋል።

በ2016 በጀት አመት በአስተዳደር ደረጃ 5.1 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ በታቀደው መሰረት በስድስት ወሩ መሰብሰብ ካለበት 3.1 ቢሊዮን ብር 2.3 ቢሊዮን ብር ለመሠብሰብ ተችሏል ይህም ከእቅድ አንፃር የተሻለ አፈፃፀም ነው ብለዋል።

ከተለያዩ ምንጮች 420 ሚልዮን ብር በተያዘው አመት ለመሰብሰብ መታቀዱን እና በስድስት ወሩ 240 ብር ለመሰብሰብ ቢታቀድም 212 ሚሊዮን ብር በመገኘቱ ለትምህርት ጥራት ማስጠበቂያ(ጂቲፒ) እና ለከተማ ልማታዊ ሴፍትኔት ለሚከናወኑ ስራዎች እንዲሁም መሰል ተግባራት እንዲውሉ ተደርጓል በዚህም በስድስት ወሩ 96% አፈፃፀም ያመላከታል ሲሉ ምክትል ቢሮ ኃላፊው ገልፀዋል ።

በአስተዳደሩ ከሚሰበሰበው 5.1 ብሊዮን ብር እና ከፌደራል የሚመጣ 1.9 ቢሊዮን ብር በጥቅሉ 7 ቢሊዮን ብር ሀብት በፋይናንስ አስተዳደሩ ተቋሙ የሚያከናውን ሲሆን ይህም በስድስት ወራት አፈፃፀሙ 96% ፋይናንሱ ለታለመለት አላማ እንዲውል ከማድረግ አንፃር ጥሩ ክንውኖች መኖራቸውን ጠቅሰዋል።

በአስተዳደሩ እየተከናወኑ ያሉ ፕሮጀክቶች በታለመላቸው ጊዜና በጀት እንዲከናወኑ የፕሮጀክቶች አፈፃፀም የሚከታተሉ ሶፍትዌሮች ለምተው በአስተዳደሩ እየተከናወኑ ያሉ 124 ፕሮጀክቶች እቅድና አፈፃፀማቸውን በአግባቡ በዚሁ ሶፍትዌር ክትትል እየተደረገ ይገኛል ሲሉ ምክትል ቢሮ ኃላፊው ገልፀዋል።

የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ያረጋግጣሉ ተብሎ በአስተዳደሩ በተለያዩ የልማት ስራዎችን የሚያከናውኑ አምስት የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ከአንድ አመት እስከ አምስት አመት በአስተዳደሩ የልማት ስራ የሚያከናውኑ መኖራቸውንም ገልፀዋል።

ባለፉት ስድስት ወራት እንደ ተቋም የገጠሟቸው ተግዳሮቶችንም ሲገልፁ ከውጭ የሚመጡ ፋይናንስ በጊዜ አለምጣት አፈፃፀሙም ላይ ክፍተት ማምጣቱን እና የእቅድና ሪፖርት አሰራር ላይ በተያያዘም በእውቀትና ክህሎት ባለመሰራቱ ክፍቶች መኖሩን በቀጣይ ስራዎች በመስራት የተሻለ አፈፃፀም እንዲኖር ይደረጋል ብለዋል።

**በትዕግስት ቶሎሳ**

**ፎቶ፡-አብይ ሽመልስ**

# በምግብ ደህንነት ላይ የሚመክር የውይይት መድረክ ተካሄደ



በአስተዳደሩ ከተለያዩ የአለም ሀገራት የተውጣጡ የድሬዳዋ ልጆች እና ወዳጆች እንዲሁም ከኒጀር ፣ ከማሊ ፣ ከፈረንሳይ እና ጅቡቲን ጨምሮ ከሌሎች ሀገራትም የመጡ የዲያሎግ ሂዩማኒቲ አባላት እና ተሳታፊዎች ከድሬዳዋ ዩኒቨርስቲ ጋር በመተባበር ያላቸውን ልምድ እና እውቀት የሚያካፍሉበት በምግብ ደህንነት ላይ የሚመክር የውይይት መድረክ ተካሄደ፡፡

የውይይት መድረኩ በዋናነት የአስተዳደሩን የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት በማጠናከር ልምዶችን እውቀቶችን በመቅሰም ወደ ነባራዊ ሁኔታዎች በመቀየር የአስተዳደሩን ልማት ለማፋጠን ታሳቢ ያደረገ የውይይት መድረክ መሆኑ ነው የተገለጸው፡፡

በውይይት መድረኩ ላይ ተገኝተው የመክፈቻ ንግግራቸውን ያደረጉት የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ዶ/ር ኡባህ አደም መድረኩ ድሬዳዋን በሰፊው ሊያስተዋውቅ የሚችል እና በርካታ አዎንታዊ ገጽታ ለመገንባት መልካም አጋጣሚ የሚፈጥር መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ውይይቱ የማህበረሰቡን ቁልፍ ችግር በመፍታትም ረገድ ሀገር በቀል እውቀቶችንና ልምዶችን በማሳደግ በኩል ትልቅ አቅም የሚፈጥር መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ከተለያዩ ዓለም ሀገራት ከመጡት የድሬዳዋ አስተዳደር ልጆች፣ ወዳጆች ፣ የዲያሎግ ሂዩማኒቲ አባላት እና ተሳታፊዎች ጋር በትምህርት፣ በጤና፣ በግብርና እና በሌሎች ዘርፎች የልምድ ልውውጥ ማድረጉ ለአስተዳደሩ ከፍተኛ ጥቅም እንደሚያስገኝ የገለጹት ደግሞ የከንቲባው ማህበራዊ ዘርፍ አማካሪ የሆኑት አቶ ኡመር አህመድ ናቸው፡፡

ውይይቱ በተለያዩ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚ ጉዳዮች ላይ የሚመክር መሆኑን ያነሱት አቶ ኡመር የአሁኑ እና የወደፊት ትውልዶች በጋራ የመሻሻል ፍላጎት እና በጋራ መስራት ባህልን መሠረት ለመጣል አስተዋጽኦ ያላቸው በምግብ ራስን መቻል፣ የአየር መዛባትና ተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ፣ ምጣኔ ሀብት፣ ዲፕሎማሲ፣ ወጣቶች፣ ሴቶች፣ ትምህርት እና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ውይይቶች በቀጣይ ጊዜያት በልኡካን ቡድኑ የሚከናወኑ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

**በሰላም ለማ**

**ፎቶ፡- ሙሉዓለም ደሴ**

## ርዕሰ - አንቀጽ

# ምኒሊክ ተወልዶ ባያነሣ ጋሻ ' ግብሩ እንቁላል ነበር ይሄን ጊዜ አበሻ

የአድዋ ድል የኢትዮጵያ ብሔራዊ ክብር ማኅተም፤ የጥቁር ህዝቦች የነፃነት ተጋድሎ ቀንዲል ነው፡፡ የመላው ዓለም ተፈጥሮአዊ ግብር እና ሰብአዊ ክብር የታደሠው፤ በእውነትና በፍትህ ህልውናና ምልዓት ላይ የተሰካ ትልቅ ጥርስ የተነቀለው ... በአድዋ የታላቅ ህዝቦች ታላቅ ድል ነው፡፡

ከአዲስ አበባ ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ ስንሄድ 1066 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ታላቁ ጦርነት የተደረገበትና ታላቁ ድል የተገኘበት ሥፍራ አድዋ ከተማና የከተማው ግድም ገመገሞች ይገኛሉ፡፡ በኢትዮጵያውያን አቡሻኽር (Julian calendar) የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም፤ ወይም በአውሮጳውያን የዘመን አቆጣጠር (Gregorian Calendar) February (የካቲት) መጨረሻ እና March (መጋቢት) መጀመሪያ ላይ 1896. ለጦርነቱ መነሻ የሆነው ውል የተፈፀመው በዚሁ ዘመን ከአዲስ አበባ በስተሰሜን 468 ኪሎ ሜትር ርቀት ግድም ከውጫሌ ከተማ ግርጌ ከአምባሰል ተራራ ሥር ወሎ ውስጥ ንጉሥ ይስማ እየተባለ በሚጠራ ሥፍራ ነው፡፡

ሸልዶ ተራራ ወይም (ሶሎዳ ተራራ)፤ ማርያም ሸዊቶ፤ አዲ ተቡን፤ ረቢ አርእየኒ (እግዚሃር አሳየኝ)... በመሠኘት የሚታወቁት እነዚህ ገመገሞችና ተራራማ ሥፍራዎች ዋነኞቹ የጦር ግንባሮች ናቸው፡፡ በመቶ ሺህ የሚሠላ የኢትዮጵያ ገበሬ ሠራዊት ከአንድ ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የአውሮጳ ቅኝ ገዢ ወራሪዎችን ድባቅ ከመታና ረግጦ ካስወጣ በኋላ ከምሽቱ አራት ሰዓት ግድም (የካቲት 23 ቀን) እንዳማርያም ላይ ተሰባስቦ በአንድ እግሩ ቆሞ ቀኙን (ድሉን) ለሰጠው አምላክ ምሥጋና አቅርቧል፡፡ አባት ሆይ፤ ንቀውን የመጡ የአገራችንን ድንበርና ልዕልና የደፈሩ የአውሮጳ ኮሎኒያሊስት ወራሪዎችን እንድናሸንፍ (ድል እንድናደርግ) ስለረዳኸን እናመሰግንሃለን ...

ሃያ ዘጠኝ ሺህ ፈረሰኞችን ጨምሮ ከመቶ ሺህ እስከ መቶ ሃያ ሺህ የሚገመት አንድ ሺህ ኪሎ ሜትር በባዶ እግሩ የተጓዘ የኢትዮጵያ የገበሬ ሠራዊት በወታደራዊ አካዳሚ የሠለጠነውን የአውሮጳ ወራሪ ጦር የካቲት 23 ማለዳ አሥራ አንድ ሰዓት ግድም ገጥሞ ከረፋዱ አራት ሰዓት ላይ ማሸነፉን አረጋግጧል ይለናል የታሪክ ተመራማሪው ጆርጅ በርክሌይ የአድዋ ጦርነትና ዳግማዊ አፄ ምኒሊክ በተሰኘና ዳኘው ኃይለሥላሴ ወደ አማርኛ በተረጐሙት መጽሐፉ ላይ፡፡ የኢትዮጵያ ገበሬ ሠራዊት ፈረሱ ላይ ሆኖ የጋሻውን እምብርት መሬት ላይ እያጠቀሰ ጐራዴውን አየር ውስጥ እየቀዘፈ ባበደ መንፈስ (በተቆጣና በቆረጠ መንፈሥ) በጀግንነት ተዋግቷል፡፡

ጦርነቱ በተጀመረ ከአምስት ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ሃምሣ ስድስቱም የኢጣሊያ መድፎች ሙሉ ለሙሉ ተማርከዋል፤ የቅኝ ገዢውን ወራሪ ሠራዊት ከመሩት ጀኔራሎች ጄኔራል አልቤርቶኒ ሲማረክ የሠራዊቱ ዋና አዛዥ ጄኔራል ባራቴሪ ከጥቂት አጃቢዎቹና በሽንፈት ከተበታተኑ የኢጣሊያ ወታደሮች ጋር ሸሽቷል፡፡

በዚህ ድብልቅልቅ ያለ ውጊያ ከሃምሣ ስድስቱ የኢጣሊያ መድፎች በተጨማሪ ብዙ ሺህ ቀላልና ከባድ መትረየሶች እንዲሁም የነፍስ ወከፍ ጠመንጃዎች በአሥር ሺሆችና በመቶ ሺዎች ከሚቆጠሩ መሰል ጥይቶቻቸው ጋር ተማርከዋል፡፡ በአጠቃላይ ምርኮው ወደ አዲስ አበባ የተጓጓዘው በአምስት መቶ አጋሰሶች ተጭኖ ነው፡፡

በማግስቱ የካቲት 24 ቀን 1888 ዓ.ም ከጠዋቱ አራት ሰዓት ላይ የኢጣሊያ ምርኮኞች በምኒሊክ ድንኳን ፊት ሲያልፉ የኢትዮጵያ ጀግና የገበሬ ሠራዊት እየፎከረ እየሸለለ አሳልፋዋቸዋል፡፡ ጄኔራል አልቤርቶኒ በምርኮኛነት ኢትዮጵያ ውስጥ ቆይቶ አገሩ ከተመለሰ በኋላ በፃፈው መጽሐፍ ላይ ከሚፎክሩት ጥቁር የነፃነት ተዋጊዎች መሃከል አንዱ እንደ እኛው ነጭ አውሮጳዊ ነው ብሎአል፡፡ ይህ ሰው ከፈረንሣይ አገር ወደ ኢትዮጵያ ለጦር መሣሪያ ጥገና የመጣ ካፒቴን ኦርዲናንስ ሲሆን፤ አሁን ጊዜው የጦርነት ስለሆነ ወደ አገርህ ተመለስ ቢባል ቢሠራ አሻፈረኝ ብሎ ከእኛ ጋር አድዋ ድረስ የዘመተ ነው፡፡

ኢትዮጵያ በአድዋ ጦርነት ላይ ከተዋጋችባቸው የጦር መሣሪያዎች ሠማንያ ሺህ የሚሆኑት አሮጌ ጠመንጃዎች የተገዙት ከፈረንሳይ አገር በምሥጢር ነው፡፡ ጠመንጃዎቹን ገዝተው ወደ ኢትዮጵያ ያስገቡት ለመጀመሪያ ጊዜ መኪና ወደ ኢትዮጵያ ያስገቡት በሥጋ በደምና በትውልድ አርመናዊ በነፍስና በመንፈስ በዜግነትና በልብ ፍቅር ኢትዮጵያዊ የሆኑት የኢትዮጵያ የልብ ወዳጅ ሰርኪስ ቴሪዝያን ናቸው፡፡

አሁን በመዲናችን የሚገኘው የአርሾ ላቦራቶሪ ባለቤትና በዓለም ላይ ኢትዮጵያን የመሰለ ውብ አገር የለም ያሉኝ ዶክተር አርሻቪር ቴሪዝያን ኢትዮጵያ ውስጥ አርመናዊ ትውልድ ኖሮት ኢትዮጵያዊ ዜግነት የሌለው (ኢትዮጵያዊ ያልሆነ) አርመን ያለመኖሩን ያጫወቱኝ ከአሥራ አምስት ዓመታት በፊት ነው፡፡ የሠማንያ ሺህ ጠመንጃዎቹን አገዛዝ ሁናቴ የሚያውቁት ደግሞ ከአርሾ ቀደም የሚሉትና ከአሥራ ስድስት ዓመታት በፊት ለሪፖርተር ጋዜጣ ይሄንኑ በአንደበታቸው የገለፁት አቬዲስ ቴሪዝያን ናቸው፡፡ ሠርኪስ ቴሪዝያን ጠመንጃዎቹን ከገዙ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ያስገቡት በጅቡቲ በኩል ነፋስ ባህሩን ሲያነሳና እንደ ግድግዳ ሲያቆም በዚያ ተፈጥሮአዊ ክንውን በመጠቀም ደብቀውና ሸሽገው ነው፡፡

የአድዋ ድል ለመጀመሪያ ጊዜ የተከበረው በሠባተኛ ዓመቱ በ1895 ዓ.ም (እ.ኤ.አ በ1903) ከአንድ መቶ ዘጠኝ ዓመታት በፊት አሁን ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ያለበት ሥፍራ ምኒሊክ አደባባይ ነው፡፡ በክብረ በዓሉ (በድል በዓሉ) ላይ ዲፕሎማቶችና የውጪ አገር መንግሥታት ተወካዮች አርበኞች የመንግስት ባለሥልጣኖች ብዙ ሺህ ፈረሰኞችና ሥፍር ቁጥር (ወፈ ሠማይ የሆኑ) ኢትዮጵያውያን ከሊቅ እስከ ደቂቅ መገኘታቸውን፤ ከፈረሰኞቹ ብዛት የተነሳ ፀሐይ በአቧራ እስከመጋረድ መድረሷን ጳውሎስ ኞኞ የኢጣሊያና የኢትዮጵያ ጦርነት በተሰኘ መጽሐፉ ላይ ጽፎአል፡፡ እንዲሁም ተክለፃዲቅ መኩሪያን የመሳሰሉ ኢትዮጵያውያን የታሪክ ተመራማሪዎችና የውጪ አገር ዜግነት ያላቸው ፀሐፍትና ተመራማሪዎች በተለያዩ መፃሕፍቶቻቸው ይሄንን አሣምረው ጽፈውታል፡፡

ታላቁ የጥቁር ህዝቦች ድል (የአድዋ ድል) በመላው ዓለም ፖለቲካ ላይ ከፍተኛና ዋነኛ ለውጦች አምጥቶአል፡፡ የእንግሊዝ ጋዜጦች በአድዋ ድል ማግስት የዓለም ታሪክ ተገለበጠ ታላቅ የትውልድ ኃይል በአፍሪቃ ተቀሰቀሰ ... ብለው ፃፉ፡፡ በኢንሳይክሎፒዲያ ብሪታኒካ፡- ዘመናዊት ኢትዮጵያን የፈጠረ የተባሉት ዳግማዊ ዓፄ ምኒሊክ በሌሉበት (እርሳቸው በአካል ባልተገኙበት የነፃነት ተጋድሎ መሪዎች ጉባኤ) የአፍሪቃና የመላው ዓለም ጥቁር ህዝቦች የነፃነት ተጋድሎ መሪ ተደርገው ተመረጡ፡፡

## አጀንዳ

# ዓለማቀፋዊው የአድዋ ድል

ከ125 ዓመት በላይ ያስቆጠረው የአድዋ ድል ጥቁሮች በቅኝ ግዛት ውስጥ በነበሩበት ወቅት፣ ኢትዮጵያ ያለማንም አጋዥነት ጣልያንን ድል ማድረጓ በወቅቱ በመላው ዓለም የተለዬ ተፅዕኖ መፍጠሩ ይነሳል፡፡

ድሉ ቅኝ ገዥዎች አፍሪካን ያዩበት የነበረውን መነጽር የቀየረ ከመሆኑም በላይ፣ በመላው ዓለም ያሉ ጥቁሮችም ለነጻነት የሚያደርጉትን ተጋድሎ በተለዬ ኹኔታ አጧጡፈው እዲቀጥሉ ያደረገው ኢትዮጵያ አድዋ ላይ ጣልያንን ድል ካደረገች በኋላ መሆኑን የታሪክ ድርሳናት ይገልጻሉ፡፡

ድሉ በዓለም አቀፍ ደረጃ በጸረ-ቅኝ ግዛት ትግሉ የተጫዎተው ሚና የጎላ ቢሆንም፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ ግን የሚገባውን ያህል ቦታ እየተሠጠው አይደለም የሚሉ አሉ፡፡

የአድዋ ድል የአፍሪካ በዓል እንዲሆን እና በዓለም ላይ ያሉ የነጻነት ታጋዮችም ቀኑን እንዲዘክሩት በማድረጉ ረገድ ኢትዮጵያ የሚገባውን ያህል አለመሥራቷን በማንሳት ብዙዎች ወቀሳ ያቀርባሉ፡፡

የአድዋን ድል ዓለመረ አቀፋዊ ይዘት፣ እንዲሁም የድሉን ምንነት ባለሙያ በማናገርና የተለያዩ መዛግብትን በማገላበጥ የአዲስ ማለዳው ሳሙኤል ታዴ የሐተታ ዘ ማለዳ ርዕሰ ጉዳይ አድርጎታል፡፡

የአድዋ ድል ለኢትዮጵያውያን የነጻነት ጉዳይ ሲሆን፣ ለሌሎች አፍሪካውያን እና በመላው ዓለም ለሚገኙ ጥቁሮች ግን እንደ ሠው መቆጠርንያሳዬ መሆኑን ምሁራን ይናገራሉ፡፡

ብዙ ጥቁሮች ከዚያ ቀድሞ ራሳቸውን እንደ (ነጻ)ሠው ለመቁጠር ይቸገሩ የነበረውነጮ ቅኝ ገዥዎቻቸውትክክለኛ የሠው ፍጥረት እኛ ነን በማለት ይሰብኳቸውና ራሳቸውን እንደ ሠው እንዳይቆጥሩ ያስፈራሩዋቸው ስለነበር ነው የሚሉ መረጃዎች አሉ፡፡

በዚህም ኢትዮዮጵያ ከነጭ ወራሪ ጋር ጦርነት ለማድረግ ማቀዷ ሳይቀር ያስደንቃቸው ነበር፡፡ በጦርነቱም ወቅትኢትዮዮጵያየነጭ ወታደር ገድላ እና ማርካ ነጻና ሉዓላዊት አገር መሆኗን ሲያዩ፣ በመላው ዓለም ያሉ ጥቁሮች እሷን አብነት በማድረግ ሠው መሆናቸውን ከመቁጠር ባለፈ ለነጻነታቸው መታገል እንደጀመሩ ታሪክ ያወሳል፡፡

ከኹለት መቶ ዓመት በላይ በቅኝ ግዛት ከኖሩት ደቡብ አፍሪካውያን የተገኙት ኔልሰን ማንዴላም፣ ለነጻነት ትግል እንቅስቃሴያቸው ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት ሱዳን በደረሱ ጊዜ ካዩት ነገር እጅግ ያስገረማቸው ጥቁር አውሮፕላን አብራሪ ኢትዮጵያውያንን ማየታቸው እንደሆነ በወቅቱ ገልጸው እንደነበር ይነገራል፡፡

እንዲሁም፣ከአድዋ ድል በኋላ በርካታ የአፍሪካ አገራትም የኢትዮጵያ ሠንደቅ ዓላማ ቀለማትን በተለያየ መልኩ መጠቀማቸው የድሉ ውጤት መሆኑን ታሪክ አዋቂዎች ያስረዳሉ፡፡

በዋልታ ሚዲያ ኮርፖሬሽን ከፍተኛ የጥናት ባለሙያ የሆኑት ተረፈ ወርቁ የአድዋን እና አፍሪካዊ ዕሳቤን በተመለከተ ለአዲስ ማለዳ በሠጡት ማብራሪያ፣የአፍሪካን ታሪክ፣ ቅርስና ባህል አካቶ የያዘው ፓን አፍሪካኒዝም ዕሳቤ ከአድዋ በፊት የነበረ ነው፣ ሆኖም ግን የአድዋ ድል ለእንቅስቃሴው ትልቅ ጉልበት ሆኗል ነው ያሉት፡፡

የፓን አፍሪካኒዝም ዕሳቤ በጃማይካና በካረቢያን አገሮች የተጀመረ መሆኑን አንስተው፣ ኢትዮጵያኒዝም በሚባለው ዕሳቤ ውስጥ ጎልተው የሚጠቀሱት ጃማይካዊው ማርከስ ጋርቬይና አፍሪካ አሜሪካዊው ዊሊያምድ ቦይ (Father of Pan Africanism)ደግሞ የአድዋን ድል በላቀ ኹኔታ ለፓን አፍሪካኒዝም እንቅስቃሴመስፋፋት እንደተጠቀሙበት አመላክተዋል፡፡

በዚህም፣ አውሮፓውያን አፍሪካ ባህል፣ ቅርስ፣ ታሪክ እና የራሷ አስተዳደር የሌላትየጨለማ ምድር አድርገው ይቆጥሯት ስለነበር፣ በእነ ማርከስ ጋርቬይ እንቅስቃሴ ውስጥየኢትዮጵያ ሥልጣኔ ከግሪክና ከሮም ሥልጣኔ አቻ ነው የሚለውን የጥንታዊ ግሪኮችን ጽሑፍ በመጠቀም እና የአድዋን ድል በማንሳት ለቅኝ ገዥዎችን ምላሽ ይሠጡ እንደነበር ጠቅሠዋል፡፡

የድሬዳዋ አስተዳደር የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ በየሳምንቱ የሚታተም **ሚያዚያ 21/1996 ዓ.ም** ተጀመረ

ረቡዕ -የካቲት / 20 / 2016 ዓ.ም

ድሬ ጋዜጣ

**አዘጋጆች**
በድሉ ኃይሌ
ማቲያስ አንዳለ
እስከንድር ኡስማን

**ፎቶ ግራፈር**
ሰላም አበበ

**ዋና አዘጋጅ**
ሔለን ሽጉጤ
( 09 20 26 49 55 )

**ሌይአውት ዲዛይን**
ሰማን ሙስጠፋ

**የኮምፒዩተር ፅሁፍ**
አለም አስጨናቂ

ስልክ - 025 111 6065
ፋክስ - 025 111 4972 ፖ.ሳ.ቁ 370
ኢ-ሜይል - Info pubbure@yahoo.com
ዌብሳይት - www.direcomm.gov.et
ፌስቡክ - Dire Dawa Geovernement Communication Affairs Bureau (@DDGCAB)

# ለታሪክ...

በስንታየሁ እንግዳ

በዓለማችን በኦቲዝም የሚጠቁ የሰዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱን የ CDC/ The Centers for Disease Control መረጃዎች ያሳያሉ እንደ CDC/ The Centers for Disease Control መረጃ ከሆነ ከዓለም ሕዝብ 1 በመቶ ያህሉ የኦቲዝም ተጠቂ ነው፡፡ ይህም ማለት ደግሞ ከአጠቃላይ ሕዝብ 75 ሚሊዮን የሚሆኑት የችግሩ ሰለባዎች ናቸው ማለት ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ እንደ ጎርጎሮሳውያኑ አቆጣጠር በ 2022 ከ 100 ሰው አንዱ የኦቲዝም ተጠቂ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በአሜሪካ በ 2023 ብቻ ከ36 ህፃናት አንዱ በኦቲዝም ሰለባ ሆኗል፡፡ ከመላው ዓለም ከፍተኛ የኦቲዝም ተጠቂዎች ያሉባት ሀገር ኳታር ስትሆን ዝቅተኛውን የኦቲዝም ተጠቂ ቁጥር ያስመዘገበችው ደግሞ ፈረንሳይ ነች፡፡ ወንዶች ከሴቶች ልጆች ይልቅ በኦቲዝም የመያዝ ዕድላቸው ከፍተኛ ሲሆን ከሴቶች በ አራት እጥፍ እንደሚልቅ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

በአሜሪካ የኦቲዝም ችግር ላለባቸው ህፃናትና አዋቂዎች የሚወጣው የህክምናና ስልጠና ወጪ በአማካይ ኦቲዝም ተጠቂ ካልሆኑት ሰዎች ከ4.1 እስከ 6.2 እጥፍ ብልጫ አለው ይህ ማለት ደግሞ ለችግሩ የተሰጠውን ልዩ ትኩረትን የሚያሳይ ሲሆን በአገራችን የተሰጠው ግምት ደግሞ በአንፃሩ እጅጉን አናሳ የሚባል ነው፡፡ እጅግ በጣም ትንሽ ትኩረት ከተሰጣቸው ጉዳዮች መካከል ተከትሎ ደግሞ ችግሩ ያለባቸው የልጆች ቁጥር እጅግ እየጨመረ ይገኛል፡፡ ለምሣሌ፡- በመንግስት ደረጃ በእነዚህ ልጆች ላይ ትኩረት አድርጎ ማዕከል በመክፈት የተለያዩ ስልጠና ወይም ቴራፒ በመስጠት የሚሠራ እስካሁን የለም፡፡ እስካሁን የተቋቋሙት የኦቲዝም ማዕከላት በወላጆች ብርታትና ፅናት ነው፡፡

ኦቲዝም ማለት ከአዕምሮ አሠራር ወይም ከአንጎል አሰራር ጋር ግንኙነት ያለውና በልጆች ዕድገት ላይ የሚከሰት እክል ነው (Neoro developmental disorder)፡፡ ኦቲዝም በሰዎች ህይወት ከሚገጥሙን ፈተናዎች አንዱ ነው፡፡ በኛ ሀገር በገጠሩ አካባቢ ባህላዊ ሆኖ የአዕምሮ ችግር ያለበት ቤተሰብ በጣም ያፍራል በዘራቸው ይሄ በሽታ አለ ከተባለ ሌሎቹ ልጆች ህይወት ላይ መጥፎ ነፀብራቅ ይኖረዋል በማለትና አንዳንዴም የእርግማን ውጤት እንደሆነ ይታሰባል፡፡ በከተማም ቢሆን እንደሌላው በሽታ እኩል ታይቶ ሊታከምና ግልፅ ማድረግ ባይፈልጉም መጠነኛ ለውጥ ግን አለ፡፡ ቤተ እምነቶች በተለይ በዚህ ጉዳይ ላይ ወላጆች ለልጆቻቸው እንዲራሩ ማስተማር አለባቸው፡፡ ኦቲዝም እርግማን አይደለም በፈጣሪ ቁጣም የሚመጣ ጉዳይ አይደለም ወይም ወላጆች ያጠፉት የተሳሳቱት ነገር ስላለ፣ ለልጆቻቸው ያላደረጉት ነገር ስላለ የሚፈጠር ጉዳይ አይደለም ነገርግን በተለየ መንገድ ልጆች ልዩ ሆነው ይመጣሉ እንደማህበረሰብም እንደ ወላጅም እነዚህ ልጆችን ልዩነታቸውን አክብሮ መቀበል አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡ በመጨረሻም እነዚህ ልጆቻችንን የተለያዩ ቦታዎች ላይ ማሳተፍ አስፈላጊ ነው፡፡ ለምሣሌ ልደት፣ መዝናኛ፣ ቤተ-እምነት እና የተለያዩ ጨዋታዎች ውስጥ ከልጆች ጋር እንዲቀላቀሉ ማድረግ፡፡

ወላጆች ማድረግ ያለባቸው በመጀመሪያ ልጁ ከሌሎች ልጆች የተለየ ነው ብሎ መቀበል የልጆችን ወርቃማ ጊዜ ሳያባክኑ(ሳያሳልፉ) ቶሎ በፍጥነት መርዳት ውጤታማ ያደርጋል ወላጆች ሰው ምን ይለኛል ከማለት (ይሉኝታ) ከመካድ ቶሎ ወደሐኪም በመውሰድ ተገቢውን እገዛና



**ወ/ሮ ሰናይት በቀለ**

**የለታሪክ ኦቲዝም ማዕከል መስራች**

ስልጠና አግኝተው ከዕድሜ ልክ ጥገኝነት ልጆቻቸውን ቢታደጉ ኦቲዝምም ሆነ ሌሎች የዕድገት እክሎች (የቋንቋ መዘግየት፣ ቨርቹአል ኦቲዝም ብዙ ሰዓት ቲቪና ሞባይል በማየት የሚመጣ የኦቲዝም ዝርያ፣ ኦቲዝም፣ የአዕምሮ ዕድገት ውስንነት እና ዳውን ሲንድረም የመሳሰሉትን የአዕምሮ ዕድገት እክሎች እንደማንኛውም አካላችን አዕምሮም የሚታመምና የሚታከም በመሆኑ የተለያየ ረጅም ጊዜና ትዕግስት የተሞላበት ህክምና ቴራፒዎች ከማዳን ጀምሮ መለወጥና መሻሻል እንደሚችሉ የዘርፉ ባለሞያዎች ይመሰክራሉ፡፡ ነገር ግን ለውጡም የሚለካው ቶሎ በጨቅላነት ተገቢውን ህክምና በሙሉ በሰጠናቸው መጠንና ኦቲዝሙ (ዕድገት እክሉ) በልጆቹ ላይ እንዳስከተለው የጉዳት መጠን ይወሰናል ይሉናል የዘርፉ ባለሞያዎች።

ለታሪክ ኦቲዝም ማዕከል ቦርድ መር አገር በቀል የበጎ አድራጊ ድርጅት ሲሆን አመሰራረቱም ጠንካራ መሰረትና ዘላቂ እንዲሆን በማሰብ ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት ያላቸው ባለድርሻ አካላት ከሆኑት ከት/ቢሮ፣ ከሴቶችና ህፃናት ቢሮ፣ ከጤና ቢሮ፣ ከድሬዳዋ ብዙሃን መገናኛ ድርጅት በአካል ጉዳተኞች ላይ ከሚሠራ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት በልዩ ፍላጎት ላይ ዕውቀትና የሞያ ልምድ ያላቸው ምሁራንን አካቶ የተመሰረተ ድርጅት ነው፡፡ ወደ ድሬዳዋ ስንመጣ ደግሞ የኦቲዝም ማዕከልም የለም የልዩ ፍላጎት ቴራፒ ማዕከልም የለም ነገር ግን በከተማው ውስጥ በኦቲዝም ጥላ ስር ያሉ ልጆቹ አሉ ችግሩም እንዳለ ነው፡፡ በመሆኑም ለነዚህ ልጆቻችንና ወላጆቻቸው ለታሪክ ኦቲዝም ማዕከል መመስረቱ ያለው ጠቀሜታ አጠያያቂ አይደለም፡፡

የልዩ ፍላጎት ት/ት የእያንዳንዱ ተማሪ ፍላጎት ብቃት፣ ችሎታ እንደ ልጆቹ ችግር ዓይነት መሰረት አድርጎ ስለሚሠራ መንግስት በቅርብ ጊዜ የጀመረው አካቶ የተባለው የት/ት አሰጣጥ ምንም እንኳን በተለያየ የልዩ ፍላጎት ውስጥ ያሉትን ልጆች ከመደበኛ ተማሪዎች ጋር በመቀላቀል ማስተማር መጀመሩ አበረታች ቢሆንም በተለይ ደረጃ 3 ኦቲዝም ያለባቸው ምግብ የሚመርጡና ለዓመታት ከአንድ ወይም ከሁለት ምግብ ውጪ የማይበሉ መሆናቸው፤ የተዛባ የእንቅልፍ ችግር 24 ሰዓታት ሙሉ የማይተኙ፤ ከተኙም እኩለ ለሊት ተነስተው የሚጮሁ፤ የሚጫወቱ፣ የሚያለቅሱና የሚስቁ ወዘተ እረፍት አልባ መሆናቸውባለማቋረጥ ራሳቸውን መንከስ፤ ጭንቅላታቸውን ከግድግዳ ጋርና ከመሬት ጋር ማጋጨት፤ እጃቸውን አፋቸው ከተው የሚያስመልሱ፤ኤሌትሪክ፤ ገደል፣ የመኪና መንገድ፤ መርዝ አይለዩም፡፡

ህይወታቸውን ጉዳት ላይ የሚጥላቸውንም ካለማወቅና ካለመለየታቸው በተጨማሪ ከቤት ወጥተው መጥፋትና መናገር ካለመቻላቸው ጋር ተደማምሮ ልጆቹ ትልቅም ሆኑ ትንሽ ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው ናቸው፡፡ በተለየ ሁኔታ (በኦቲዝም ማዕከል) የተለያየ ድጋፍና ስልጠና፤ለ1 ልጅ እንደ ኦቲዝሙና በልጁ ላይ እንዳመጣው ጉዳት መጠን አንድ መምህር ስለሚያስፈልገው አካቶ ት/ት ቤቶችም ለነዚህ ልጆች በቂና ተገቢ የሆነ እርዳታና ድጋፍ (የተለያዩ ቴራፒዎች) ለመስጠት ይቸገራሉ፡፡ ልጆቹም ሌሎችን ልጆች የሚያውክ ባህሪያት ስለሚኖራቸው የመማር ማስተማሩን ሂደት ሊያስተጓጉሉ ስለሚችሉ ት/ቤቶችም ለነኚህ ልጆች ክፍት አይደሉም፡፡ በመሆኑም በድሬዳዋ የተቋቋመው ለታሪክ ኦቲዝም ማዕከል እነኚህ ልጆቻችን ከዕድሜ ልክ ጥገኝነት ለማዳን ከተዘጋባቸው ቤትና ከታሰሩበት ለመፍታትና ወደ ብርሃን ለማውጣት ማዕከሉ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ ማዕከሉ 10 አገልግሎቶችን በአንድ ጊቢ ውስጥ ይሰጣል ጠቅለል ስናደርገው በዋነኛነት 5 ተግባራትን ያከናውናል፡፡

1. እነኚህ ልጆቻችን በቃላትም ሆነ በምልክት መግባባት እንዲችሉ (speech therapy)
2. እራሳቸውን መርዳት እንዲችሉ (Occupational therapy)
3. አስቸጋሪ የሆኑ ባህሪያትን አጥፍቶ ወይም ቀንሶ መልካም በሆነ ባህሪ መተካት (ABA)
4. የስሜት ቅንጅት (Sensory Integration)
5. የምግብና የጤና ህክምና (Biomedical intervention)

ለታሪክ ኦቲዝም ማዕከል ልጆቹን የተለያዩ ቴራፒዎችን ሰጥቶ ህይወታቸው እንዲቀየር ከማድረግ በተጨማሪ ወላጆች ላይ ትልቅ ሥራ ይሠራል፡፡ ወላጆች ያልጠበቁት ነገር ሲገጥማቸው ስሜታቸው ስለሚጎዳ ጠንካራ ስነ-ልቦና እንዲገነቡ ተከታታይ የሆነ በባለሞያ የሚሰጥ የምክር አገልግሎት እና ልጆቻቸውን ቤት ውስጥ የሚያሰለጥኑበትንና የሚረዱበትን የተለያዩ የቴራፒ ስልጠናዎችን እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም ከጤና ቢሮ ጋር በመተባበር እነዚህ ልጆች መታወቂያ ተሰርቶላቸው በተለየ ሁኔታ ቅድሚያ ተሰጥቷቸው ስለልጆቻችን ባህሪ (ስለ ኦቲዝም) በሚያውቅ ሃኪም አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

እነዚህ ልጆች በማዕከሉ ሰልጥነው ለውጥ አምጥተው ወደ መደበኛ ት/ቤት መሄድ የሚችሉትን ወደ መደበኛ ት/ቤት መላክ፤ በት/ት ብዙም መግፋት ያልቻሉትን የተለያዩ የእጅ ሞያ በማሰልጠን የሞያ ባለቤት ማድረግ ወላጆችም ልጆቻቸውን ቀኑን ሙሉ ተቀብለን ስናውልላቸው የራሳቸውን ሥራ መሥራት እንዲችሉ ያስችላቸዋል፡፡ ሌሎችም በድርጅታችን ውስጥ ለመሥራት የሚያስችል ሞያ ያላቸውን በመቅጠር በድርጅቱ በሚሰጥ የተለያየ ቴራፒ አግኝተው ድርጅቱንም በቤት ውስጥ ደግሞ ልጆቻቸውንም ለተሻለ ውጤት ማብቃት የሚችሉ ይሆናሉ፡፡

ለታሪክ ኦቲዝም ማዕከል ከመንግስት፣ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም ከባለሃብች ከድርጅቶች የምንጠብቃቸው ድጋፎች መካከል ዋናውና የመጀመሪያው እነኚህን ደረጃ 3 የሆነ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ልጆችና የት/ቤት ደጃፍ የተዘጋባቸው፤ በቤት ውስጥ ታስረው ያሉበትን የጨለማ ህይወትና የወላቻቸውን የዕድሜ ልክ ጫና ለማገዝ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡና ማዕከሉን በሁለት እግሩ ቆሞ ተገቢውን ድጋፍ ለነኚህ ልጆች እንዲሰጥ ከድርጅቱ ጎን በገንዘብም ሆነ በቁሳቁስ እንዲቆም ነው፡፡ ከማህበረሰቡ የሚጠበቀው ያለው በገንዘቡ፣ በዕውቀቱና በጉልበቱ ወዘተ ማዕከሉን ቢረዳ ትውልድ ተሻጋሪ የሆነ ለብዙ ልጆችና ወላጆች መፍትሄ የሚሆን አሻራውን እንዲያሳርፍ ከላይ ለነበረው ፅሁፍ ሙሉ መረጃዎችን ያጋሩኝ የለታሪክ የኦቲዝም ማዕከል በድሬዳዋ መስራች ወ/ሮ ሰናይት በቀለ፡፡

## በጥንታዊቷ. . .

ከገጽ 1 የዞረ

ወደ ድሬዳዋ በጋራና በርብርብ ማምጣት ከተቻለ በመስተዳድሩ የሚታየውን የቤት ችግር በብዙ እንደሚቀርፍ ጠቁመዋል።

አቶ ገበየሁ አያይዘውም ዘመናዊና አስተዳደሩን የሚመጥን ጥራት ያለው የጋራ መኖሪያ ቤቶችን በመገንባት ለነዋሪዎች በማድረስ ሂደት ውስጥ በአስተዳደሩ የሚገኙ ባለሀብቶችን ጨምሮ ሁሉም የሚመለከተው አካል የራሱን አስተዋፆ እንዲያበረክት ጥሪ አቅርበዋል።

በመድረኩ ከአዲስ አበበ ከተማ አስተዳደርና አዳማ ከተማ የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎች ቀርበው ከመድረኩ ሀሳብና አስተያየት ተሰቶበት ውይይት ተደርጎበታል።

የመድረኩ ተሳታፊዎች በበኩላቸው የቤት ጉዳይ አንገብጋቢ መሆኑንና ችግሩን ለመፍታት የሌሎች ከተሞች ተሞክሮዎች መቅረባቸው ጥሩ መሆኑን ገልፀው፤ የቤት ጉዳይ የጋራ በመሆኑ ርብርብ እንደሚያስፈልገውና በዚህም የበኩላቸውን እንደሚወጡም ተናግረዋል።

መንግስትም ያለውን ቦታ በአግባቡ ተጠቅሞ ለማህበረሰቡ ቤት ማቅረብ ላይ ሊሰራ መሆኑ ሊጠናከር የሚገባው ስራ መሆኑ ከመድረኩ የተነሳ ሲሆን፤ የሚገነቡት ቤቶችም ደረጃቸውን የጠበቁና እስማርት ሲቲን ያገናዘቡ እንዲሆኑ በማድረግ ለመስተዳደሩ ጥሩ ገፅታን እንዲያላብሱ ማድረግ ይገባል ሲሉ ተሳታፊዎቹ ሀሳባቸውን ሰጥተዋል።

**በኤደን ሳሙኤል**

**ፎቶ፡-አብይ ሽመልስ**

## የድሬዳዋ . . .

ከገጽ 1 የዞረ

እንዳለ ተናግረዋል ።

በየትኛውም ሀገራት ላይ የማይገኙ ቅርሶች ኢትዮጲያ ሀርላ ላይ እንደተገኙና በተለይም አብዛኛው ጥናትና ምርምሮችም በራስ ሀይል የሀገር ልጆችና በእንግሊዛዊው ፕሮፌሰር የበላይ መሪነት እየተጠና ያለ በመሆኑ ስራውን ልዩ እንደሚያደርገው የሀርላ አርኪዮሎጂስት ጥናት ቡድን አባል የሆነው የዶክትሬት ተማሪ ተመስገን ለታ ተናግሯል ።

**በአለማየሁ አበበ**

# ፈተና ሳይበግራት ከራሷ አልፎ ለብዙኃን እንጀራ የሆነችው ስራ ፈጣሪ

በዳግማዊ ፍቃዱ



መቅድም፡- የሰው ልጅ ተፈጥሮ ከአራቱ ባሕርያተ ሥጋ ማለትም ከነፋስ፤ ከእሳት፤ ከውሃና፤ ከመሬት ሲሆን አምስተኛ ነፍስን ጨምሮ እነዚህ በአንድ ሰው የሕይወት ዘመን ላይ ሲንፀባረቁ ይኖራሉ፡፡

ከሃያ እስከ አርባ ያለው የዕድሜ ክልል የእሳት ባሕርይ ጎልቶ የሚታይበት ነው፡፡ ይህም ዘመነ እሳት ወይም ምግበ እሳት ይባላል፡፡ ይህም ሰውን ወጣት የሚያሰኘው ዘመን ነው፡፡

በዚህ የወጣትነት ዘመናችን ጥሩና ታላቅ መሆን ካልቻልን የምናጣው ክብርን ብቻ ሳይሆን ማንኛውንም ኃላፊነት ጭምር እናጣለን፡፡ በእርግጥም በወጣትነት ዘመን የሚገኝ ምኞት እጅግ ከፉ ሊሆን ይችላል፡፡ ሆኖም ወጣትነት የሚሠራበት ዘመን እንጂ ከፉ ምኞት የሚመኙበት ዘመን መሆን እንደማይገባ ዕሙን ነው፡፡

በወጣትነት ዘመን የሚገኝ ምኞት ከመጠን በላይ ወደ ጥፋት የሚስብ የሚጎትትና የሚያታልል ነው፡፡ ነገርግን ለወጣትነት ፈተና መጋፈጫ ፍቱን መፍትሔው እራስን ማወቅና እራስን መግዛት እንደሆነ የስነ-ማህበራዊ ዘርፍ ተመራማሪዎች ያስረዳሉ፡፡ለራሳችን ያለንን አመለካከትና ጠባይ በአጠቃላይ ከሌሎች ሰዎች የሚለየንንና የሚያመሳስለንን ማንነት በመረዳት በዓላማ መኖር ስንችል ራሳችን ማወቅ ቻልን ማለት ነው፡፡

ራሱን የሚያውቅ ሰው ስብዕናውን ያከብራል፤ ለምን ዓላማ እንደተፈጠረ በመረዳት ስብዕናውን ጠብቆ በደስታ ይኖራል፤ በራሱም ይተማመናል፡፡ የሚያውቀውን በአግባቡ ይናገራል፤የማያውቀውን ይጠይቃል፤ ድክመቱን ሲነግሩት በአዎንታዊ መንገድ ይቀበላል፤ ማንነቱን በቦታና በጊዜ ራሱን አይለዋውጥም የጸና ግንብ ነው፤ በዐለት ላይ ተመሥርቷልና፡፡ ከሐሜት ይርቃል፤ በግልጽ መወያየትን ያዘወትራል፤ ለውድቀቱም ራሱን ተጠያቂ ያደርጋል፤ ሌሎቹን ተጠያቂ አያደርግም፤ ለውድቀት በቀላሉ እጁን አይሰጥም የሚጓዝበትን ያውቃልና፡፡

ከታላላቆቻችን ካለፈው የወጣትነት ሕይወታቸው ልምድ በመውሰድ አሁን ያለበትን ሁኔታ በመረዳት ይረዳል፡፡ ራሱን የሚያውቅ ወጣት ለህይወቱ መሳካት አስፈላጊውን መሥዋዕትነት ይከፍላል፡፡ ራሱን ያላወቀና ያልገዛ ወጣት ዓላማውን ይስታል፤ ለራሱም ለሌሎችም መሆን አይችልም፡፡

ይህንን ሃሳብ ለማንሳት የወደድኩት ባለፉት ተከታታይ የድሬየጋዜጣ እንግዳችን አምድ እንዳስቃኘናቹ ታታሪና እራሳቸውን ገዝተው በወጣትነት ዕድሜያቸው ሰርተው አትርፈው ለሌሎችም ባላቸው አቅም የዕለት ጉርስ ማግኛ ስራ መፍጠር የቻሉ ወጣቶች ሁሉበዛሬው እትማችንምየጥረት ታሪኳ ከአፍ አልፎ ልብን የሚሞላ ወጣትን ለማስቃኘት ስለአሻኝ ነው፡፡

በአስተዳደራችን በጥቃቅንና አነስተኛ በግልም ሆነ በማኅበር ተደራጅተው በመሰማራትበተለያዩ አካላት እገዛና የራሳቸውን ጥረት አክለው የተሻለ ደረጃ የደረሱ ከራሳቸው አልፈው ለሌሎች የስራ ዕድል መፍጠር ችለው ግለሰቦች ውስጥ የዛሬ ባለታሪካችንወጣትን ለተሞክሮነት ይበቃል ብዬ በማመን ነው፡፡ የተሞክሮ ፋይዳውም ለማንኛውም ሃገር በቀል ልማት ወዳድ ዜጋ መነሣሣትን ይፈጥራል ተብሎ ይታመናል፡፡ተሞክሮ ስራ ጠባቂሳንሆን የፈጠራ አባቱ ሁነን በአጭር ጊዜ ውስጥ የሃገራችንን የለውጥ ትንሳኤ የምናይበት መሪ መንገድም ማድረግ ይቻላል፡፡"ብልህ ከሌሎች ይማራል አይደል" ብሂሉስ፡፡

ወጣት ሜሮን እንዳልካቸው ትባላለች። በትምህር ደረጃዋ እስከ ከፍተኛ ትምህርት ዘልቃለች፡፡ወጣቷ የዩኒቨርሲቲ ተመራቂ ብትሆንም የግድ በተማርኩበት ሙያ ስራ ካልያዝኩኝ ብላ የሙጥኝ አላለችም፡፡ ይልቁንም በራሷ ስራ ለመፍጠር አስባ ተንቀሳቀሰች እናም ስራ ለመስራት የሚያስችሏትን አማራጮች ማጤን ጀመረች፡፡"መፍትሔከችግሮች መንስኤ ይቀዳልናሜሮን ስራ ለመጀመር በቅድሚያ አካባቢዋ ያሉ ነገሮችን ነው የቃኘችው፡፡

በምትኖርበት አካባቢም ሆነ እንደ ድሬደዋ ጥቅም ላይ ውለው የሚጣሉ የፕላስቲክ ኮዳዎች የአካባቢን ገፅታ እያበላሹ መሆኑን ተረዳች፡፡እነዚህየፕላስቲክ ኮዳዎች የአካባቢ ገፅታን ከማጉደፍ ባሻገር በረጅም ጊዜ ሂደት የብክለት መንስኤዎች መሆናቸውን ሳይንሳዊ ጥናቶች ያስረዳሉ፡፡

ወጣቷ በመጨረሻም በየሜዳው ተጥለው የሚታዩ የፕላስቲክ ኮዳዎችን መልሶ ጥቅም ላይ በማዋል ስራ ብትሰማራ አዋጭ እንደሚሆን ተረዳች ፡፡

ወጣት ሜሮን"ሥራ ፈጠራ በትምህርት ብቻ የሚገኝ ነገር አይደለም። በቀለም ትምህርት ጎበዝ መሆን ብቻውን የራስ ሥራ ለመጀመር አይበቃም። ጥንካሬና ርዕይ፣ በራስ መተማመንና ለፈተናዎች ሁሉ ዝግጁ መሆን ያስፈልጋል። ሥራ መፍጠር ለየት ያለ አተያይ ይፈልጋል።የማህበረሰቡን ችግር ለየት ባለ መረዳት ማየት ያስፈልጋል"ትላለች፡፡

"ነገሮች የሚሳኩት መውደቅ የማንፈራ ከሆነ ነው! ወጣት በፍፁም ተስፋ መቁረጥ የለበትም!"፡፡" በተለይ ወጣት ተስፋ መቁረጥ የለበትም! ጤናም ጉልበትም ዕውቀትም የሚኖረው በወጣትነት ዕድሜ ስለሆነ መሮጥ ያለብን ይሄኔ ነው። ብንወድቅም ደግሞ ራሳችንን አንስተን ድጋሚ መሮጥ ነው እንጂ ተስፋ መቁረጥ በፍፁም አያስፈልግም፡፡ በቃ ህይወት ይቀጥላል!"ይህ የወጣት ሜሮንየህይወት መርሆዎች ከሆኑት አንዱ ነው፡፡

ወጣቷየወዳደቁ የፕላስቲክ ኮዳዎችን መልሶ ጥቅም ላይ የማዋል ስራዋን የጀመረችው በ300 ሺ.ብር ካፒታል ነው፡፡እርግጥ ነው ገና የዩኒቨርሲቲ ተመራቂ ሆኖ ማንም ወጣት በራሱ የተጠቀሰውን የብር መጠን ለስራ ማስኬጃነት በራሱ ላይኖረው ይችላል፡፡ለሜሮን ወደስራ ለመግባት የሚያስፈልጋትን ብር ለማግኘት ቤተሰብ ድጋፍ እንዳደረገላት ለመረዳት እንችላለን፡፡

ምንም እንኳን አሁን ላይ የወጣቷ ስራ በተሞክሮነት የሚገለፅ ደረጃ ላይ ለመድረስ ቢችልም ሁሉም ነገር አልጋ በአልጋ እንዳልነበር በትዝታ መለስ ብላ ታስታውሳለች፡፡"ስራ ፈጣሪነት ማለት በሚቻለው መንገድ ብቻ ሳይሆን በማይቻለውም ማለፍ መቻል ነው፡፡ በስራ ፈጣሪነት አለም ውጣ ውረዶች በዝተው ተስፋ አስቆራጭ ነገር ቢያጋጥም እንኳን ዋናው ነገር ዓላማን ማሰብ እና ተስፋ አለመቁረጥ ተገቢ ነው፡፡ እውነት እንነጋገር ከተባለ ደግሞ እንኳን ስንጀምር ይቅርና አሁንም ሁሉም ነገር ሙሉ አይደለም፡፡ በስራ ፈጣሪነት ዓለም ውስጥ ሁሌም ውጣ ውረድ እና ፈተና አለ፡"፡፡የሚያልሙትን ነገር ካልሞከሩ በስተቀር መሳካት አለመሳካቱ አይታወቅም ፡፡"

ሰው የትኛውንም ያህል ተሰጥኦ ቢኖረው ጠንካራ ሰራተኛ ካልሆነ እንዲሁም ወደሚፈልገው ህልም የሚወስደውን መንገድ ተነስቶ ካልጀመረ ስኬታማ አይሆንም፡፡ ስኬት ደግሞ ግዴታ ትልቅ ገንዘብ ማግኘት አልያም ትልቅ ቦታ ላይ መቀመጥ ብቻ አይደለም! ወደ ህልማችን የሚወስደንን መንገድ ተነስተን ጀመርን ማለት ስኬታማ ለስኬታችን በር እየከፈትን ነው ማለት ነው፡፡ሜሮን በስራዋ ጉዞ ያጋጠሟትን ችግሮች ብሎም በብልሃትያለፈቻቸውን ውጣ ውረዶች በትዝታ ታወሳዋለች፡፡

ዛሬ ወጣቷ 9 የሚሆኑ ቋሚ ሰራተኞች በስሯ አሉ፡፡ከቋሚ ሰራተኞች በተጨማሪ የፕላስቲክ ኮዳዎችን ሰብስበው ከሚያቀርቡ ግለሰቦች ጀምሮ በተለያዩ የስራ ደረጃዎች ላይ ለተሰማሩ 50 ለሚሆኑ ግለሰቦች የስራ ዕድል መፍጠር ችላለች፡፡

ወጣቷ ስራዋን አሁን ካለበት ደረጃ ይበልጥየማሳደግ ህልም አላት፡፡የፕላስቲክ ኮዳዎችን ሰብስቦ ለማከማቸት የሚያስችላት የቦታ ጥበት ችግር እንዳለባት የምትናገረው ወጣቷ ስራዋ የፕላስቲክ ኮዳዎች አጥቦ ፤ አፅድቶ እንዲሁምበማሽን ጨፍልቆወደ ሌሎች ምርቶች ለማዋል በሚችልበት ደረጃ ማዘጋጀትን የሚጨምር በመሆኑ ሰፋ ያለ የመስሪያ ቦታን ይጠይቃል፡፡

በመሆኑም ነገሮች ከተመቻቹላት ማለትም ስራዋ የሚፈልገውን ያክል የቦታ ጥበት ችግር ከተቀረፈላት የመስሪያ ማሽን በመጨመር ስራዋን በማስፋት አሁን ከምታቀርበው የአገር ውስጥገበያ በተጨሪ እስከ ወደውጪ የመላክዕቅድ እንዳላት ትገልፃለች፡፡

የወጣት ሜሮን የስራ ጉዞ ለበርካቶች ተሞክሮ የሚሆን ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ በተለይ "ለጀማሪ ስራ ፈጣሪነት የአዕምሮ ዝግጁነት ያስፈልጋል !"፡፡

የስራ ፈጣሪነት ጉዞ በጣም ፈታኝ እንደሆነ አይቼዋለሁ፡፡ ቀላል መንገድ አይደለም! በተለይ ለጀማሪ ስራ ፈጣሪዎች ማለት የምፈልገው ነገር የአዕምሮ ዝግጁነት ያስፈልጋል ነው፡፡ ምክንያቱም ጀማሪ ስራ ፈጣሪ ሲኮን የሚፈለገው ነገር ሁሉ ተሟልቶ አይኖርም፡፡ ብዙ የሚገድቡ ነገሮች ይኖራሉ፡፡ የቢዝነሱ ፈጣሪም፣ ሽያጭ ባለሞያም ፣ የፋይናንስ ባለሞያም መሆን ሊያስፈልግ ይችላል የስራ ፈጣሪነት መንገድ ቀላል እንዳልሆነ እና የአዕምሮ ዝግጁነት እንደሚያስፈልግ መታወቅ አለበት፡፡ማንም ሰው በፈጠራ ችሎታው ወይም ልዩ በመሆኑ ማፈርም ሆነ ከመስራት ወደ ኋላ መቅረት የለበትም፡፡

ምናልባት "በእኛ ሀገር ሁኔታ ወጣትና ሴት ተኾኖ ስራ ፈጣሪነት ቀላል ላይሆን ይችላል"የማምረቻ ኢንዱስትሪው በብዛት በወንዶች የተያዘ ነው፡፡ ወጣት ሲኮን ደግሞ እንደልብ ከባንክ ብድር የማግኘት ዕድሉ ጠባብ ነው፡፡ ከምንም በላይ ደግሞ በዘርፉ ቀድሞ የገባ/ች ወይም በስራው በደምብ ልምድ ያዳበረ/ች መካሪ ከሌለ ጉዞው የበለጠ ፈታኝ ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ እንደ ወጣት ሜሮን ያሉ ታታሪና እራሳቸውን ገዝተው በወጣትነት ዕድሜያቸው ሰርተው አትርፈው ለሌሎችም ባላቸው አቅም የዕለት ጉርስ ማግኛ ስራ መፍጠር የቻሉ በርካታ ስራ ፈጣሪዎች ለስኬታችን ጉዞ መማሪያ መሆን ይችላሉ ብዬ አስባለሁ፡፡ለዛሬ አበቃው ሳምንት እስከምንገናኝ በቸር ቆዩኝ፡፡

# የሴቶችን ጥቃት ለመቀነስ ግንዛቤ እንፍጠር !

በሔኖክ ይልማ

በኢትዮጵያ ውስጥ ስለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ሴቶች የተደረጉ ጥናቶች በእጅጉ ውስን ናቸው። ነገር ግን ብዙ አስተዋይ ግለሰቦች ኢትዮጵያውያን ሴቶች በህይወት ዘመናቸው ምን አይነት አስቸጋሪ ኑሮ እንደሚኖሩ አስተያየቶቻቸውን አቅርበዋል በተለይም ደግሞ በገጠር አካባቢ የሚኖሩ፡፡ ታዲያ ኑሮን አስቸጋሪ ከሚያደርጉባቸው አድካሚ ሥራዎች መካከል በየዕለቱ ረጅም መንገድ እየተጓዙ እንጨትና ውሃ ማመላለስ፣በእጅ መፍጨት፣ የቤት ውስጥ ሥራ ማከናወን፣ ልጆች መንከባከብ ይገኙበታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በተለምዶ ከሚደርስባቸው ልዩ ልዩ ተፅዕኖዎች በተጨማሪ ራሳቸውን በማጠናከር ረገድ በትምህርትና በሥራ ቅጥር ላይ ከወንዶች ያነሰ ዕድል ነበራቸው፡፡

በኢትዮጵያ ከሰማኒያ አምስት በመቶ በላይ የሚሆኑት ሴቶች ከእጅ ወደ አፍ በሆነ የእርሻ ሥራ በሚተዳደሩ የአርሶ አደር ቤተሰቦች ውስጥ በገጠራማ አካባቢ ይኖራሉ። የገጠር ሴቶች ደግሞ ሰፊ የሰው ጉልበት በሚጠይቀውና ሕጻናትን ጨምሮ ሁሉም ሰው አድካሚ የጉልበት ሥራ ከሚሠራበት የገጠሩ የግብርና ኢኮኖሚ ጋር የተቆራኙ ናቸው፡፡ ሥር በሰደደው የቆየ ባሕላዊ እምነት የተነሳ የመሬት ስሪት ማሻሻያውም የሴቶችን የተቀጠሪነት ደረጃ አላሻሻለውም። የሴቶች በኢኮኖሚ ሁኔታዎች መለወጥ ምናልባት የኑሮ ደረጃቸውን ያሻሽል ይሆናል። እውነተኛውን ለውጥ ለማምጣት ግን በሴቶች ላይ ያለንን ሥርዓተ ጾታ አመለካከት ወደ ተሻለ ደረጃ ማሸጋገርን ይጠይቃል፡፡

## ፆታዊ ጥቃት ምንድን ነው?

ጥቃት በጥሬ ትርጉሙ በተለያዩ መልኩ የሚፈጸምና በሰዎች አካል፣ ህይወት እና ንብረት ላይ ጉዳት የሚያደርስ ድርጊት ነው፡፡ ሃይል፣ አቅም/ስልጣን/፣ ነጻ ፈቃድ እና ሰብዓዊ መብት፤ ጥቃት ሲነሳ አብረው የሚነሱ መገለጫዎች ናቸው፡፡ በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጥቃት ማለት ደግሞ ፆታን መሰረት ያደረገና አካላዊ፣ ወሲባዊ ወይም ስነ ልቦናዊ ጉዳት በሴቶች ላይ ሊያደርስ የሚችል ማንኛውም ድርጊት፣ ማስገደድ ወይም ተገቢ ያልሆነ ነጻነትን የማሳጣት ተግባር የሚያጠቃልል መሆኑን የሚገልጽ ነው፡፡ ይህም በሴቶች የግል ህይወትም ሆነ በማህበራዊ ኑሮ ላይ ሊደርስ የሚችል እንደሆነበተለያዩ ድንጋጌዎች ተቀምጧል፡፡

በሴቶች ላይ የሚደርስ ጥቃት የተለያየ ነው፡፡ የኢፌድሪ ጠቅላይ ዐቃቢ ህግ በ2008 ዓ/ም በሴቶች እና ሴት ህጻናት ላይ የሚፈጸም ጾታዊ ጥቃት እና የሴቶች መብት በሚል አርዕስት ባወጣው ፅሁፉ በሴቶች ላይ የሚደርሱ የጥቃት አይነቶችን ዘርዝሯል፡፡ በስፋት የሚታወቅ የጥቃት ዓይነት የቤት ውስጥ ጥቃትሲሆን በቤት ውስጥ እና በቤት ውስጥ ጉዳይ ምክንያት የሚፈፀም ማንኛውም ጥቃት ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ በኃይል፣ በቃላት እና በምልክት፣ በአካል ላይ፣ በሞራል እና ስነ ልቦና እንዲሁም በማንኛውም መንገድ ነፃነትን በሚጋፋ ሁኔታ የሚፈፀም ጥቃትን ያካትታል፡፡ ምሳሌ፤ቀላልና ከባድ አካል ጉዳት፣ ስድብ፣ ዛቻሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

ኢኮኖሚያዊ ጥቃት ደግሞ በማንኛውም መንገድ የንብረት እና የኢኮኖሚ መብት መጋፋት ወይም መንፈግን የሚያካትት ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ሴቶችና ሕፃናት ንብረት ወይም ሃብት እንዳያፈሩ እና በንብረታቸው እንዳያዙ በማድረግ የንብረት ባለቤትነት መብታቸውን በማሳጣት ለሰሩት ሥራ ተገቢውን ክፍያ ባለመስጠት በጥገኝነት እንዲኖሩ ማድረግ ይገለጻል፡፡ምሳሌ፡ ጉልበት ብዝበዛ፣ የጋራ ንብረትን /ሀብት ተጠቃሚ አለመሆንን ይጠቀሳሉ፡፡

ሌላኛው ጥቃት አካላዊ ጥቃት ሲሆን በማንኛውም መንገድ በአካል ላይ የሚፈፀም የሃይል ጥቃት ነው፡፡ ለምሳሌ መምታት፣ መገፍተር፣ መተንኮስ እና እስከ ግድያ ያለውን ያጠቃልላል፡፡ ወሲባዊ ጥቃት ደግሞ ኃይልን በመጠቀም በሌላ ሰው ላይ ያለፍላጎቷ/ቱ የሚፈፀም ማንኛውም የወሲብ ድርጊትና የወሲብ ድርጊትን የመሰሉ ትንኮሳዎችን ያጠቃልላል፡፡ ለምሳሌ አስገድዶ መድፍር፣ የወሲብ ንግድ፣ ፆታዊ ትንኮሳ፣ ግብረ-ሰዶምና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ሥነ ልቦናዊ ጥቃት ፣ ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ጥቃቶችም በሴቶች ላይ ከሚደርሱ የጥቃት አይነቶች ውስጥ የሚካተቱ ናቸው፡፡

## በተጨባጭ እየታየ ያለው ምንድን ነው?

ባለፉት ጊዜያት ለጆሮ የዘገኑ፤ ልብ የሰብሩ፣ አንገት ያስደፉ፤ ለሰሚም ለነጋሪም የከብዱና ሰቀጣጭ ጥቃቶች፤ እንደ ማህበረሰብ ለሴቶች የሚሰጠውን ቦታ ፍንትው ያደረጉ ጥቃቶች ተስተውለዋል፡፡ እነዚህ ጥቃቶችም ፆታን መሰረት ያደረጉ እና ሙሉ ለሙሉ ለማለት በሚያስደፍር መልኩ በታዳጊ ልጃገረዶችና በሴቶች ላይ የሚደርሱ ናቸው፡፡

በቤት ዉስጥም ሆነ በዉጪ የሚፈጸሙ ማስፈራራት፤ ማስገደድ፤ ነፃነትን መቀነስ፤ መገደብ፣ ድብደባ፤ የወሲብ ትንኮሳ፤ አስገድዶ መድፈር፤ በሴቶች አካል መነገድ፤ ያለዕድሜ ጋብቻ፤ ግርዛት ፣ስድብ እና ማዋረድ፤ ጠለፋ እና የሃይል ጋብቻ የመሳሰሉት በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ፆታዊ ጥቃቶች ናቸዉ፡፡

ሴት ከቤት ስራዎች ጀምሮ የተለያዩ ስራዎችን የምትሰራ ቢሆንም ስራዋን ቀለል ሚያደርግላት የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ካለማቅረብ ባሻገርም በማህበረሰቡና በቤቷ በተለያዩ ዘርፎች ጫና ያድርባታል፡፡ በመሆኑም አካላዊና ስነ ልቦናዊ ጥቃቶች በየጊዜው እንዲሰነዘርባት ሆኗል፡፡ኢትዮጵያ ዉስጥ በሴቶች አካልም ሆነ ስነ ልቦና ላይ የሚፈፀመው ጥቃት የድሮ ታሪክ ሳይሆን አሁንም ያለ መሆኑን የሚያመላክቱ የተለያዩ መረጃዎች እየወጡ ናቸው፡፡

ከወራት በፊት ጥቃቱ ስር ስለመስደዱ ይፋ ያደረገና በሴቶች ላይ የሚሰነዘርን ፆታዊ ጥቃት የሚያወግዝ ሰልፍ በትግራይ ክልል መቀሌ ከተማ ተካሂዶ እንደነበረም ይታወሳል፡፡ የክልሉ ሴቶችና ህፃናት ጉዳዮች ቢሮ በትግራይ ክልል ፆታዊ ጥቃትን በተመለከተ እየተስተዋሉ ያሉ ችግሮች በእርግጥም ጥቃቱ ጨምሮ ነው ወይስ ጥቃቶች ለሚመለከታቸው የህግ አካላት ሪፖርት ማድረግ ነው የሚለው ጥናት እንደሚያስፈልገው ይናገራል፡፡ ሆኖም ግን በተለይም አስገድዶ መድፈር በትግራይ ክልል እየጨመረ መሆኑን ቢሮው ገልጿል፡፡፡፡

የሴቶች ህፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴር ፆታዊ ጥቃት ያለበትን ወቅታዊ ሁኔታ ለማወቅ ጥልቅ ጥናት መደረግ አለበት ባይ ነው፡፡ ሆኖም እ.አ.አ በ2016 በተገኘ መረጃ በሀገሪቱ 23 በመቶው የሚሆኑ ሴቶች ፆታዊ ጥቃት ይደርስባቸዋል፡፡ ከዚህ ውስጥ 68 በመቶው በትዳር አጋር የሚደርስ ጥቃት ነው፡፡ ሆኖም ግን ጥቃቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ መልኩን እየቀየረና እየተባባሰ መምጣቱን ሚኒስቴሩ ያምናል፡፡ የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማሕበር ከሁለት ዓመታት በፊት ይፋ ባደረገው መረጃ የጥቃቱ ሰለባዎች በሁሉም የኑሮ ደረጃ እና የኅብረተሰብ ክፍል ዉስጥ የሚገኙ ሴቶች ናቸው ይላል። ማሕበሩ በአንድ ዓመት ዉስጥ ከትዳር ጋር የተገናኙ 3 ሺህ 754 አቤቱታዎችን አስተናግዶ፤ 2 ሺህ 105ቱ በሴቶች የተፈፀሙ ጥቃቶች የሚያሳዩ ናቸዉ።

አሁን ላይም በኢትየየጵያ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች በመበራከታቸው አንገብጋቢ ችግር ሆኗል፡፡ ችግሩ የማህበራዊ ቀውስ ቢሆንም በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ያደረገው ደግሞ የተንሻፈፈ አስተሳሰብ ነው፡፡ አዲስ ማለዳ የ2016ቱን የኢትዮጵያ የስነ ሕዝብና ጤና ዳሰሳን በዋቢነት እንዳቀረበው፤ 68 በመቶ ሴቶችና 28 በመቶ ወንዶች ባል ሚስቱን ቢመታ አግባብ ነው ብለው ያምናሉ፡፡

የአንድ ህብረተሰብ መሠረት እንደሆኑ የሚነገርላቸው ሴቶች የመብታቸው ጉዳይ ፤ ማህበራዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ እንዲሁም የፖለቲካ መብቶቻቸዉን ሁሉ ያካትታል። በዚህ ረገድ ያሉ መብቶቻቸዉ ሙሉ በሙሉ እንዳይከበሩ ታዲያ የማሕበረሰቡ አመለካከት አሁንም እንቅፋት ሆኖ መቀጠሉን የሴታዊ አራማጆች ይገልፃሉ፡፡ ፆዊታ ጥቃት ለማህበረሰቡ አንገብጋቢ ቀውስ መሆኑን የሚጠቅሱት አራማጆቹ፤ መፍትሄው ላይ የማይሰራ ከሆነም ሴቶች ካላቸው ፋይዳና ሚና አንፃር ዙሪያ መለስ ችግር ይገጥመናል ይላሉ፡፡

በማህበረሰቡ ዘንድ ፆታን መሠረት አድርገዉ የሚፈፀሙ ጥቃቶች ቀጥታ ምክንያታቸዉ ማህበረሰቡ የፆታን እኩልነት አስመልክቶ ካለዉ የተዛባ አመለካከት ጋር ይያያዛል ሲሉም ያሰምሩበታል፡፡ይህም ሴቶች ላይ የተለያዩ ጥቃቶች እንደሚፈፀሙ ትልቅ ስፍራ ይዟል ይላሉ የመብት ተሚጋቾቹ፡፡

ፆታዊ ጥቃት ተበራክቶ ለመቀጠሉ የህግ ስርዓቱ መላላት በሌላ በኩል ይነሳል፡፡ በሴቶች ላይ ጾታዊ ጥቃትን ለሚፈጽሙ ወንጀለኞች ተመጣጣኝ የሆነ ቅጣት እየተሰጣቸው አይደለም የሚሉ በርካቶች ናቸው፡፡ የሚደርሰውን ጾታዊ ጥቃት ለመከላከል ተመጣጣኝ እና አስተማሪቅጣት እንዲያገኙ ማድረግለመከላከል አንዱ መንገድነው ይላሉ፡፡ ሆኖም ባለው ነባራዊ ሁኔታ ግን በሴቶች ላይ ፆታዊ ጥቃትን በሚፈፅሙ ወንጀለኞች የፍትህ ተቋማት የሚበይኑት ቅጣትተመጣጣኝአይደለም ይላሉ፡፡

የቅጣት መላላቱ እንዳለ የሚያምነው ህግ አስፈፃሚው መንግስት፤ ምንም እንኳ ጠንካራ እርምጃዎች ፆታዊ ጥቃቶችን ለመከላከል አስተማሪ ቢሆኑም፤ ዘለቄታዊ መፍትሄው ግን ማህበረሰቡን ማስተማር ነው ይላል፡፡ የሴቶች መብት ሰብዓዊ መብት ነው የሚለው የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን፤ በተቋሙ የሴቶችና ህጻናት መብቶችን የሚመረምር ክፍል እንዳለው ይናገራል፡፡ ጥቃቶችን በመከላከሉ ረገድ የሚሰሩ አካላት ፆታዊ ጥቃትን የሴቶች ጉዳይና የማህበራት ብቻ አድርገው መተው ረጅም ርቀት እንዳይኬድ ማድረጉን ይገልፃል፡፡ በመሆኑም ጥቃቶችን ለመከላከል ሲያልፍም ለመቀነስ የሁሉም ባለድርሻ አካላት ቅንጅት ያስፈልጋል፡፡

ባለፉት ዓመታት የሚፈፀሙ ጥቃቶችን ለመከላከል በርካታ ጥረቶች ሲደረጉ ቢታይም የሚፈለገውን ያህል ውጤት ማምጣት እንዳልተቻለም ይነገራል፡፡ ሴት እናት ናት፤ እህት ናት አክስት ናት የሚሉ ዘመቻዎች መደመጥ ከጀመሩም ውለው አድረዋል፡፡ ከችግሩ አሳሳቢነትን አንፃርም ጣጣው ለማህበረሰብና ለሀገርም የሚተርፍ በመሆኑ ፆታን መሰረት አድርገው የሚፈፀሙ ጥቃቶችን ለመከላከል በሚል የሴት ልጅ ግርዛትንና ያለ እድሜ ጋብቻን ለመከላከል ፍኖታ ካርታ ተቀርጿል፡፡ የጥቃቱ ሰለባ ለሆኑ ሴቶችና ህፃናትም ስነ ልቦናንም የጨመረ ህክምና እንዲያገኙ እንዲሁም ለፖሊስ ማስረጃም መስጠት የሚያስችል የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫና ማገገሚያ ተቋማት እየተቋቋሙ ናቸው፡፡

ሴቶች ከቤታቸዉ ጀምሮ በሥራ ቦታቸዉ፣ በትምህርት ቤቶች ወይም በሌሎች ማህበራዊ ኑሯቸዉን በሚከውኑባቸው መንገዶች ሁሉ ስድብ ፣ መጎንተልእንዲሁም የወሲብ ትንኮሳ ሰለባዎች ናቸዉ። ከዚህ የቃላት ጥቃት ባለፈም አካላዊ ጥቃቶች እንደ ድብደባ እና አሁን አሁን እየተለመደ የመጣው የአሲድ መድፋት፣ አስገድዶ መድፈርና ህይወትን መንጠቅ ስር የሰደዱ የማህበረሰባችን ገመናዎች ሆነው ቀጥለዋል፡፡ ነገር ግን ይሄን ለማስቆም የሁላችንም ርብርብ ያስፈልጋል እያልን ለዛሬ አበቃን፡፡

**መልካም ሳምንት**


## የጨረታ ማስታወቂያ

የድሬዳዋ አስተዳደር ግብርና ውሃ ማዕድን ኢነርጂ ቢሮ በ2016 ዓ.ም በጀት ዓመት በመደበኛ ሎት 1 ኮንስትራክሽን ማቴሪያል እና በሎት 2 የንብ ማርቢያ የተለያዩ እቃዎች ግዥ ለማድረግ ተጫራቾችን በጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡

- የግዢ መለያ ቁጥር DDAWMEB/GDS/012/2016
- የጨረታ ሰነዱን ብር 500 /አምስት መቶ ብር ብቻ/ ከድሬዳዋ አስተዳደር ግብርና ውሃ ማ/ኢነርጂ ቢሮ የግዢ ፋይናንስ ንብረት/አስ/ደጋፊ ስራ ሂደት መግዛት ይችላሉ፡፡
- ተጫራቾች የንግድ ፈቃድና የዘመኑን ግብር የከፈሉበትን ቲን ነምበር እና ቫት ተመዝጋቢ የሆነ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
- ማንኛውም ተጫራች ለጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ለእያንዳንዱ ሎት ብር 50,000 /ሃምሳ ሺህ ብር/ በባንክ በተመሰከረለት ጋራንቲ ወይንም (CPO) ከጨረታ ሰነዱ ጋር ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
- ተጫራቾች ሁሉ የጨረታ ሰነዱን በሰም በታሸገ ፖስታ በማድረግ ኦርጅናል እና ኮፒ በሚል ለያይተው ጨረታው ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ጠዋት 3፡00 ሰዓት ድረስ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
- ተጫራቾች የመጫረቻ ዋጋቸውን በተሸጠላቸው ሰነድ ላይ ባለው ቅጽ ብቻ ሞልተውና ማህተም አድርገው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
- ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በ15 ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ላይ በመ/ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ ይከፈታል፡፡ መ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለተጨመሪ መረጃ፡- ስልክ ቁጥር 0251-12-10-98**

**የድሬዳዋአስተዳደር ግብርና ውሃ ማዕድን ኢነርጂ በሮ**

## የጨረታ ማስታወቂያ

የድሬዳዋ አስተዳደር ግብርና ውሃ ማዕድን ኢነርጂ በሮ በ2016 ዓ.ም በጀት ዓመት በመደበኛ ላፕቶፕ ኮምፒውተር ግዢ ለማድረግ ተጫራቾችን በጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡

- የግዢ መለያ ቁጥር DDAWMEB/GDS/011/2016
- የጨረታ ሰነዱን ብር 500 /አምስት መቶ ብር ብቻ/ ከድሬዳዋ አስተዳደር ግብርና ውሃ ማ/ኢነርጂ ቢሮ የግዢ ፋይናንስ ንብረት/አስ/ደጋፊ ስራ ሂደት መግዛት ይችላሉ፡፡
- ተጫራቾች የንግድ ፈቃድና የዘመኑን ግብር የከፈሉበትን ቲን ነምበር እና ቫት ተመዝጋቢ የሆነ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
- ማንኛውም ተጫራች ለጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ለእያንዳንዱ ሎት ብር 150,000 /አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ ብር/ በባንክ በተመሰከረለት ጋራንቲ ወይንም (CPO) ከጨረታ ሰነዱ ጋር ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
- ተጫራቾች ሁሉ የጨረታ ሰነዱን በሰም በታሸገ ፖስታ በማድረግ ኦርጅናል እና ኮፒ በሚል ለያይተው ጨረታው ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ጠዋት 3፡30 ሰዓት ድረስ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
- ተጫራቾች የመጫረቻ ዋጋቸውን በተሸጠላቸው ሰነድ ላይ ባለው ቅጽ ብቻ ሞልተውና ማህተም አድርገው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
- ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በ15 ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ላይ በመ/ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ ይከፈታል፡፡ መ/ቤቱ የተሸለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለተጨመሪ መረጃ፡- ስልክ ቁጥር 0251-12-10-98**

**የድሬዳዋአስተዳደር ግብርና ውሃ ማዕድን ኢነርጂ በሮ**

# የተቀናጀ የበጋ ወራት የተፋሰስ ልማት ስራ በመስተዳደራችን

በኤደን ሳሙኤል



የተቀናጀ ተፋሰስ ለዘላቂ አረንጓዴ ልማት በሚል መሪ ሀሳብ የ 2016 ዓ.ም የተቀናጀ የበጋ ወራት የተፋሰስ ልማት ስራዎች ከተጀመረ እነሆ አሁን በርከት ያሉ ቀናትን አስቆጥሯል፡፡ በዚህም በአራቱም የገጠር ክላስተሮቻችን በሚገኙ ቀበሌዎች ስራው በተቀናጀ መልኩ አሁን ላይ እየተሰራ ሲገኝ የፕሮግራሙ መክፈቻ የሆነው ግንበቢዮአዋሌ ክላስተር አዳዳ ገጠር ቀበሌ ላይ ነበረ፡፡

የ2016 ዓ.ም የተቀናጀ የበጋ ወራት የተፋሰስ ልማት ስራዎች ሲጀምር በእለቱ በመገኘት ንግግር ያደረጉት የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ ክቡር አቶ ከድር ጁሀር በተለይም በድሬዳዋ አስተደደር ላይ የለውጥ አመራሩ ለተቀናጀ የተፋሰስ ልማት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ ሰፋፊ ስራዎችን እያከናወነ በመሆኑ እና ትላልቅ የግብርና እና ገጠር ልማት ፕሮጀክቶችን በውጤታማነት ተግባራዊ ማድረግ በመጀመሩ የአስተዳደራችን አርሶና አርብቶ አደር ማህበረሰብ በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ ማድረጉን ተናግረዋል ።

አርሶና አርብቶ አደሩ የተፈጥሮ ሀብት እንዲሁም ውሀ እና ለም መሬትን በማልማት የራሱን ምግብ ዋስትና በማረጋገጥ ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት የበኩሉን ሚና እየተወጣ ከመሆኑም በተጨማሪ ደረጃውን የጠበቀ የተለያዩ የግብርና ምርት ውጤቶችን ለውጭ ገበያ የማቅረብ አቅም እየፈጠረ መሆኑንም ክቡር ከንቲባው ተናግረዋል ።

በሀገራችን ለአረንጓዴ ልማት የተሰጠውን ከፍተኛ ትኩረት እና የተፋሰስ ልማት ስራ በየአመቱ በማከናወን ዘላቂና ውጤታማ ልማትን ለማስቀጠል የተቀመጠውን አቅጣጫ ማእከል ያደረገ የተቀናጀ የበጋ ወራት የተፋሰስ ልማት ስራዎችን ለማከናወን በዝግጅት ምእራፍ በርካታ ስራዎች መሰራታቸውን ደግሞ የድሬዳዋ አስተዳደር የግብርና ውሀ ማእድንና ኢነርጂ ልማት ቢሮ ሀላፊ የሆኑት አቶ ኑረዲን አብደላ ተናግረዋል ።

አቶ ኑረዲንለ 30 ተከታታይ ቀናት 37,927 የስራ ሀይል በተደራጀ የልማት ሰራዊት ንቅናቄ በማሳተፍ በ 5,550 ሄክታር መሬት ላይ የተለያዩ የአፈርና ውሀ ጥበቃ ስራዎችን በመስራት በአስተዳደሩ አሁን የሚታየውን የመሬት መራቆት ችግር በ 3 ነጥብ 7 ፐርሰንት ለመቀነስ በየአመቱ በጎርፍ የሚወሰደውን 48,685 ቶን ለም አፈር ለማዳን ጥረት እንደሚደረግ ተናግረዋል፡፡

በተለይም ከ 11,000 በላይ አባወራዎችን ተጠቃሚ ለማድረግ በ 4,556 ሄክታር መሬት ላይ የእርሻ ማሳ ምርታማነት የሚያሳድጉ የተለያዩ የአፈርና ውሀ ጥበቃ ስራዎች እንደሚሰሩና በ 3,750 ሄክታር መሬት ላይም የመስኖ ማሳዎችን የውሀ አጠቃቀም በማሻሻል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የመስኖ ውሀ ልማት ስራዎች እንደሚከናወኑም ነው ሀላፊው የገለፁት ።

ሰላም ጤና ይስጥልኝ ውድ የድሬ ጋዜጣ አንባቢያን እንዴት ከርማቹሀል ለዛሬ ወደ እናንተ ለማድረስ የወደድኩት ፅሁፍ ከላይ መግቢያዬ ላይ ቀንጨብ አድርጌ እንዳስነበብኳችሁ ስለ ተፋሰስ ልማት ነው እንዲሁም ይህ ስራ መሰራቱ ምን አይነት ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ እንደሚሰጠን እናያለን አብራችሁን ቆዩ፡፡

የተፈጥሮ ሀብት ልማት ሥራ ለግብርናው ዘርፍ የጀርባ አጥንት ነው። ሀገራት ወደ ተሻለ የኢኮኖሚ እድገት መሸጋገር የቻሉት የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ሥራን አጠናክረው በማልማት እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ። ደቡብ ኮሪያ ደግሞ በተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ሥራ በአብነት ተጠቃሽ ናት። የተፈጥሮ ሀብትን በመጠበቅና በማልማት፣ የአፈር ለምነትን በማሳደግ የምርት መጠን እንዲሻሻል በማድረግ የምግብ ዋስትናን ያረጋግጣል። የተፈጥሮ ሀብት ልማት ሥራ በ19ኛው ክፍለ ዘመን እንደተጀመረ ባለሙያዎች ይናገራሉ።

በሀገራችንከ1970ዎቹ ጀምሮ የተፈጥሮ ሀብት ልማት ሥራ መከናወን መጀመሩን አንዳንድ የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ፡፡ በዚህም ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ስራ በማሕበረሰቡ የነቃ ተሳትፎ እየተሠራ በመሆኑ ተጨባጭ ውጤት እየመጣ መሆኑን በተመሳሳይ ማየት ይቻላል።

ደቡብ ኮሪያ በተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ስራ ተጠቃሽ ናት፤ለውጤታማነቱ ደግሞ የማሕበረሰቡ የነቃ ተሳትፎ





ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው ይስተዋላል፡፡ በመሆኑም የተፈጥሮ ሀብት ልማት ሥራ (የተፋሰስ ሥራ) የአርሶ አደሩን የነቃ ተሳትፎ የሚጠይቅ በመሆኑ መረባረብ አስፈላጊ እንደሆነ የሚያመላክቱት ደግሞ በድሬደዋ ዩኒቨርስቲ የጅግራፊ ዲፓርትመንት መምህር የሆኑት ረዳት ፕሮፌሰር ደስታ በላይ ናቸው ፡፡የተፈጥሮ ሀብት ልማት ሥራ ግብርናው መዋቅራዊ ለውጥ እንዲያመጣ፣ የውኃ ምንጮች እንዲጎለብቱ፣ የሥራ ዕድል እንዲፈጠር፣ አረንጓዴ ልማት እንዲያድግ፣ የአፈር ለምነት እንዲጨምር፣ የባዮ ጋዝ (አማቂ ጋዝ) መጠንን እና የባዮ ማስ መጠንን (የስነ ሕይወት ስብስብን) ከፍ በማድረግ የጎላ አስተዋፅኦ እንዳለው ያብራራሉ።

መስተዳደራችን እምቅ የተፈጥሮ ሀብት ባለቤት በመሆኑ ልንጠብቀውና ልናለማው ይገባልም ብለዋል። ትልልቅና መካከለኛ ሐይቆች፣ ትልልቅ ፓርኮች፣ ብርቅየ የዱር እንስሳት፣ ጥብቅ ደኖች፣ ተራሮች፣ ግድቦችና ሌሎች ሀብቶች ትውልድ ተሻጋሪ እንዲሆኑ ጥበቃ እንደሚያስፈልጋቸው ረዳት ፕሮፌሰር ደስታ በላይ አሳስበዋል። በተለይም የመሬት መሸርሸር እንዳይከሰት በትኩረት በመሥራት ኢኮኖሚያዊ ፋይዳቸውን ማሳደግ ይገባል ብለዋል።

ረዳት ፕሮፌሰር ደስታ እንዳሉት የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ሥራ የአመራሩን ዕውቀት፣ ክህሎትና ቁርጠኝነት እንዲሁም የማሕበረሰቡን ትጋት በስፋት ይጠይቃል። ከተለያዩ ተቋማት ጋር በቅንጅትና ተናቦ መሥራትንም ይሻል። እየተሠራ ባለው ሥራም አበረታች ውጤት እየታየ መሆኑን ተናግረዋል። ይሁን እንጂ ጥራትን ጠብቆ አለመሥራት፣ ከሰው ቁጥር ጋር የተመጣጠነ የልማት መሣሪያ አለመኖር እንዲሁም የጉልበት መባከን ውስንነቶች መሆናቸውን በማንሳት፣ ሊስተካከሉ እንደሚገባቸው አመላክተዋል።

ዶ/ር ኃይሉ ክንዴ ደግሞ በድሬደዋ ዩኒቨርስቲ የአፈርና ውኃ ጥበቃ ከፍተኛ ተመራማሪ ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት ከ2003 እስከ 2014 ዓ.ም በተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ሥራ በተደረገው ጥናት የአፈር ለምነት መሻሻሎች መኖራቸውን ጥናቶች ያመለክታሉ። ይህም የአፈር ለምነቱን ለመጠበቅ ይወጣ የነበረውን የአፈር ማዳበሪያ ወጭ ዝቅ እንዲል አስችሏል ባይ ናቸው። በ92 ተፋሰሶች ላይ በተካሄዱ ጥናቶች በጥንቃቄ የተያዙ፣ ሕግና ደንብ ያላቸው፣ የተፋሰስ ኮሚቴ ያላቸው፣ ማሕበረሰቡ በስፋት የተሳተፈባቸውን በመለየት በተሠራ ጥናት የአፈር ለምነቱ በ21 በመቶ ከፍ እንዲል አግዟል ብለዋል ተመራማሪው።

ከላይ የተጠቀሱትን ነጥቦች ያላሟሉት ደግሞ የአፈር ለምነት እንደቀነሰባቸው ጥናቶች ያሳያሉ ብለዋል። ጥናቶችን ዋቢ አድርገው እንዳብራሩት፣ በዓለም በከባድ ዝናብና በጎርፍ ምክንያት በከፍተኛ ደረጃ የአፈር መሸርሸር እየተከሰተ ከስምንት ቢሊዮን ዶላር በላይ በየዓመቱ ይታጣል። ይህም 34 በመቶ የሰብል ምርት ወይም 34 ሚሊዮን ኩንታል ይታጣል እንደማለት ነው።

ይህ ደግሞ ሦስት ነጥብ ሰባት በመቶ የዋጋ ጭማሪ (የኑሮ ውድነት) እንዲኖር ምክንያት ነው ይላሉ። አርሶ አደሩ እርከንን በመሥራት፣ ችግኝን በመትከል፣ ከእንስሳት ንክኪ ነፃ በማድረግና ሕግና ደንቦችን ተከትሎ በመሥራት የምርት ጭማሪ መገኘቱን ይናገራሉ። አርሶ አደሮቹ ከራሳቸው ማሳ ጀምሮ የተፋሰስ ሥራ በመሥራታቸው የተሻለ ውጤት እየተገኘ ነውም ብለዋል።

የመሬት ለምነቱ እንዲጨምር በመሠራቱ ምርትና ምርታማነት ማደጉንም አንስተዋል። በአፈርና ውኃ ጥበቃ ሥራ እንዲሁም በደን ልማት ሥራ አርሶ አደሩ የተሻለ ለውጥ እያሳየ መምጣቱን አድንቀዋል። ተፋሰሶችን ጥቅም በሚሰጡ እፅዋቶች በመሸፈን አበረታች ሥራዎች ተከናውነዋል ብለዋል። በተፈጥሮ ሀብት ልማት ሥራ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በቅንጅት አርሶ አደሩን በተጠናከረ መልኩ ማገዝ ተገቢ እንደሆነ አመላክተዋል። ማሕበረሰቡን ለማገልገልና ግብርናውን ለማሻገር በጋራ ተናቦ መሥራት ይጠይቃልም ብለዋል።

በአጠቃላይ የተፋሰስ ልማት ስራዎች መንግስታዊ መዋቅሩን ጨምሮ ከባለሙያ እስከ አርሶ አደሩ ሁሉንም አስተምሯል። በመስተዳደራችን በገንደ ፈልማ ገጠር ቀበሌ ተገኝተን ያነጋገርናቸው አርሶ አደሮችምስለስራው እንዲ ብለውናል፡፡አርሶ አደር ማሜ አብዲማህበረሰቡን ባሳተፈ አግባብ በተሰሩ ስራዎች የተራቆቱ ደኖች አገግመዋል፣ የተጋጋጡ እና የተጎራረዱ የወል መሬቶች ከመሸርሸር ድነዋል፤ ምንጮችም ጎልብተዋል ብሎናል።

ከልቅ ግጦሽ የተጠበቁ የወል መሬቶች ላይ መኖ በማልማት፣ ከብቶቻቸውንም አስረው በመመገብ ዘርፈ ብዙ ጥቅሞች ማግኘታቸውን ተናግረዋል። በእርከንና መሰል የተፋሰስ ስራዎችም ምርታማነትን ማሳደግ፣ የጓሮ አትክልትና ፍራፍሬ በማልማትም የገበያ ሰብሎችን ማልማትና አመጋገባቸውን ማሻሻል እንደቻሉ ጠቅሷል። ሂደቱ አልጋ በአልጋ ባይሆንም የወል መሬቶችና የተከለሉ ደኖችን ከልቅ ግጦች በመጠበቅ ዕድርን መሰል ባህላዊ አደረጃጀቶችን በመጠቀም ጥብቅ የቁጥጥር ስርአት እንዳዳበሩ አንስተዋል።

በዚህም የአካባቢው ማህበረሰብ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና የተፋሰስ ስራዎችን ጥቅም በመረዳቱ የአስተሳሰብ ለውጥ ስለማምጣቱ ነው የሚመሰክሩት። በተፋሰሱ ነዋሪ አርሶ አደሮች ከብት አስሮ መመገብ በመቻላቸው የመኖ እጥረት ስለመቀረፉ፣ እንስሳትን አደልቦ በመሸጥም ውጤታማ መሆናቸውን ከተሳታፊ አርሶ አደሮች መካከል የሆነው ወጣት ሙክታር መሀመድይናገራል።

ከዚህም ባለፈ በችግኝ ጣቢያዎችና በሌሎች የአካባቢ ጥበቃ ስራዎች ብዙ ሰዎች ቋሚ እና ጊዜያዊ ስራ ዕድል እንዲፈጠርላቸው አድርጓል ብለዋል። የወል መሬቶችን በመከለል ከእንስሳት ንክኪ ነጻ በማድረግ ውጤታማ ከመሆን ባለፈም የወል መሬቶችን ለተደራጁ ወጣቶች በመስጠት ፍራፍሬ ልማት ውጤታማ እንዲሆኑ ማድረግ መቻሉን ይናገራሉ።

ከወረዳው አርሶ አደሮች መካከል አብዱላዚዝ አሚን እንዳሉት፤ ባለፉት ዓመታት ባከናወኑት የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራ የተራቆቱ መሬቶችን በማልማት የንብ ማነብ፣እንስሳት ማድለብ ፣የሰብል ምርታማነትን እንዲጨምር ምቹ ሁኔታ ፈጥሮላቸዋል። “ለመጪው ትውልድ አረንጓዴና የለማ ሀገርን ለማስረከብ እንድንችል በተለይ በአሁኑ ወቅት የተፋሰስ ልማት ስራችንን አጠናክረን ቀጥለናል” ብለዋል።

የተፋሰስ ልማት ስራ የአካባቢ መራቆትን ከመከላከል ባለፈ ደርቀው የነበሩ ምንጮች መልሰው መመንጨት ጀምረዋል ያሉት ደግሞ አዳዳ ቀበሌ አርሶ አደር ቀመር አብደላ ናቸው። በለሙ ተፋሰሶች ውስጥ የተተከሉ እጽዋቶች በመጽደቃቸውና እርጥበታማ አየር እንዲኖር በማስቻሉ የግብርና ስራን በተሻለ መልኩ በማከናወን ድርቅን ለመቋቋም እያስቻላቸው መሆኑን ነው የተናገሩት። ወጣት አቡሽ መገርሳ በበኩሉ፤ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራና በእፅዋት በተሸፈኑ ተፋሰሶች ላይ በማህበር በመደራጀት ወደ ንብ ማነብ ስራ ለመሰማራት መዘጋጀታቸውን ገልጿል።

የተፋሰስ ልማት ከሚሰጣቸው ጠቀሜታዎች መካከል አንዱ ወጣቱ ተደራጅቶ ከስራ አጥነት በመላቀቅ እራሱን እንዲችል ማድረግ ነው ብሏል።ተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ ባለሙያ አቶ ፈለቀ እሸቴ እንዳሉት፤ አርሶ አደሩ ባገኘው ግንዛቤ በመታገዝ የተፋሰስ ልማት ስራን ከዓመት ዓመት እያስፋፋ ይገኛል። አርሶ አደሩ ከሚሰማው ይበልጥ በተግባር የሚያየውን ነገር እንደሚቀበል ያነሱት አቶ ፈለቀ በአሁኑ ወቅት ከልማቱ የተሻለ ምርት እና ገቢም እያገኘ መሆኑን ገልጸዋል።

ውድ አንባቢያን ለዛሬ በቢዝነስ አምዳችን ስር ያዘጋጀንላችሁ ፅሁፍ ይሄንን ይመስላል ስለተቀናጀ የበጋ ወራት የተፋሰስ ልማት ስራዎች አጠር ያለም ቢሆን ግንዛቤ እንዳገኛችሁ እንዲሁም ስራው ምን ያክል ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠቀሜታዎች እንዳሉት በተጨባጭ ከመስተዳደራችን ጋር ያለውን እውነታ እንዳያችሁ ተስፋ እያደረኩ የዛሬን በዚህ አበቃሁ የሳምንት ሰው ይበለን፡፡

# ወልደ ህይወት ! !

በዘመድ ቢሆነኝ

በዓለም የፍልስፍና ታሪክ ውስጥ ጉልህ ድርሻ ይዘው የሚገኙት አውሮፓዊያን ሲሆኑ በተለይ ደሞ የሀገረ ግሪክ ፈላስፎች ናቸው፡፡ ከነሱም በተጨማሪ የመካከለኛው ምስራቋ ሀገር እስራኤል (አይሁድ ፈላስፎች) ግንባር ቀደም የሚባሉ ፈላስፎችን ለዓለም አበርክታለች(ማርክስ ፤ ኒቼ...)፡፡ ወደ ሩቅ ምስራቅ ሀገራት ስንመጣ ህንድ እና ቻይናም ለዓለም ያበረከቱት የፍልስፍና አስተዋፅኦ ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ በተለይም <existential> የተባለውን የፍልስፍና ዘይቤ ለዓለም በማበርከት ባለውለታ ናቸው፡፡

ፍልስፍና በታሪኩ በብዙ አሳቢያን የመቀንቀኗን ያህል ፤ የሰውን ልጅ ቀልብ ገዝታ ብዙ ዘመናትን የመቆየቱን ያህል በርግጥም ዓለምን በተለየ እና በሚያበለፅግ መንገድ እንድናያት እና የፍልስፍና ፍሬ በሆኑት ሀሳቦች እየታገዝን ዓለምን እንድንለውጥ ታላቅ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡ በተለይ ከነሶቅራጥስ ዘመን አንስቶ እስከ እነ ሲግመንድ ፍሮይድ ዘመን ድረስ ፍልስፍና ተፅዕኖዋ ታላቅ የሚባል ነበር፡፡ ነገር ግን ሳይንስ እያደገ ከመምጣቱ ጋር፤ ቴክኖሎጂዎች እየረቀቁ ከመምጣታቸው ጋር ተያይዞ የፍልስፍና ዋጋ እየቀነሰ መጥቷል፡፡ ዓለም ከ<ሀሳብ> ይልቅ <ቴክኖሎጂ> ላይ በማተኳሯ ፍልስፍና የቀድሞውን ዝናዋን አጥታለች ባይባልም ቀንሷል፡፡


የፅሁፌ ነጥብ ስለፍልስፍና ታሪክ እና የሌሎችን ሀገራት ተሳትፎ ለማተት ሳይሆን በፍልስፍና ታሪክ ውስጥ የሌሎችን ሀገር ተሳትፎ አይተን ስናበቃ "እኛስ"እንደ ሀገር ማን ነበረን? በድፍረት የማህበራዊ ፤ የሀይማኖታዊ ፤ የፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ግድፈት በአመክንዮ (በፍልስፍና ወይም በሀሳብ) የሞገተ አሳቢ ነበረን ወይ የሚል ጥያቄ አንስቶ ለዚሁ መልስ መስጠት ነው የፅሁፌ ነጥብ፡፡በዚህም ታሪካዊ መፅሐፍትን ለማሰስ ሙከራ አድርጊያለሁ፡፡ ይህ ነው የሚባል መረጃ ማግኘት ግን አልቻልኩም፡፡ ሆኖም ግን ከትልቅ የስንዴ ማሳ ውስጥ ቢያንስ አንዱ ፍሬ ማበቡ አይቀርምና ከብዙ ፍለጋ በኋላ በቅርቡ ታትሞ ለንባብ የበቃው <ጥበብ ከጲላጦስ ቅፅ ሁለት> መፅሐፍ ውስጥ ልብ የሚሞላ አንድ ኢትዮጵያዊ የሆነች ፍልስፍናዊ ታሪክ ለማግኘት በቃሁ፡፡የኔ ሀተታ እዚህ ላይ ይቁምና ከመፅሐፉ ወደወሰድኩት ፅሁፍ ላምራቹህ።

ፎቶ-1

መፅሐፉም እንዲህ ይቀጥላል፡- ወደ ሀገራችን የፍልስፍና አስተሳሰብ ተመልሰን እነሆ ወልደ ህይወትን አገኘነው፡፡ ወልደ ህይወት የኢትዮጵያዊው ፈላስፋ ዘርዓያዕቆብ ደቀ መዝሙርና ተማሪ በመሆን ለ59 ዓመታት ከስሩ ያልተለየ ድንቅ አሳቢ ለመሆኑ በመምህሩ ዘርዓያዕቆብ መፅሐፍ ላይ ጨምሮ ያበረከተውና የእሱን አስተሳሰብ በስፋት የታየበት ሐተታ ይመሰክራል፡፡ <ሐተታ ዘርዓያዕቆብ ፍልሱፍ> በሚለው የመምህሩ መፅሐፍ ውስጥ ተተንትኖ የቀረበልንን የወልደ ህይወት ሀሳብ ስናነብ ደግሞ በዋነኛነት የሐተታው ዓላማና ግብ ሆኖ የምናገኘው <የመጨረሻው መልካምነት> ምን እንደሆነ ነው፡፡

"እኔም ምትኩ የተባልኹ ወልደ ህይወት የመጨረሻው መልካምነት እንድታውቁ ብዬ ከመምህሬ መፅሐፍ ላይ ይኽን ትንሽ ጨመርሁ" የሚለን ወልደ ህይወት መምህሩ የነበረው ዘርዓያዕቆብ በ68 ዓመቱ ፋሲለደስ ሞቶ ዮሐንስ ሲነግስ በፃፈው መፅሐፍ ላይ የበኩሉን ጨምሮ እንዳበረከተ ይነግረናል፡፡ እንግዲህ ወልደ ህይወት ለ59 ዓመታት ከዘርዓያዕቆብ ስር ሆኖ የተማረውን <ለኢትዮጵያ ልጆች ዕውቀትና ተግሳፅ> እንዲሆናቸው አስቦ መፃፉን ከጅምሩ ሲነግረን የፍልስፍናም ዋነኛ ዓላማ ይኸው ነውና ዕውቀትና ተግሳፅ ይተርፈን ዘንድ በዚህ ዘመን እንኳን የተደረሰበት ከማይመስለው የላቀ አስተሳሰብ በመጠኑ እንቆነጥራለን፡፡

ወልደ ህይወት በአስተሳሰቡ እንደ መምህሩ ዘርዓያዕቆብ በዘመኑ ሰዎች ሀይማኖትን ለማስካድ እንደተነሳ ሰው መቆጠሩ ያልቀረለት ቢሆንም እሱ ግን ሐተታውን ሲጀምር እንዲህ ይለና፡-"ሁሉን በፈጠረና በያዘ ሁሉን በሚጠብቅና በሚመግብ ከዓለም በፊት የኖረና ያለ እስከ ዘላለምም የሚኖር ብቻውን በፍፁም ህልው የሆነ ለእርሱ ታላቅነትም ዳር ድንበር የሌለው በእግዚአብሔር ስም እፅፋለሁ!!" ይለናል፡፡ ወልደ ህይወት መፅሐፉን እንዲህ ብሎ መጀመሩ አስተሳሰቡ አንዳች ግጭት በእሱ ዘመንም ሆነ በኋላ ከሚመጣው ትውልድጋር ቢስያነሳ ከአምላኩ ሀሳብ ጋር የሚጋጭ




ጉዳይ አለማንሳቱን እንድንረዳና በዚህም ምክንያት ድፍረት መቋጠሩን የዘየደው መስሎናል፡፡

መምህሩ ዘርዓያዕቆብ "ፈርቼ የደበቅሁትን እውነት የማይፈራ ይፃፈው" በማለት ያሰፈረውን ሐሳብ ይዞ የእሱ ፍርሃት ግን አምላኩ ብቻ የመሆኑን ጋሻ አስቀድሞ አንስቶ ይመጣልናል፡፡ ይኸም ብቻ አይደለም፡ ፡ መፅሐፉ በስሜት ተገፋፍቶ ያለዕውቀት በመነዳት የመሰለውን የሚሞነጭር ስራ ፈት አልያም ዕብድ ያቀረበው ሳይሆን <ጥበብና ምርመራ እንዲሁም ተግሳፅና ፍልስፍና የደረሰው አንድ ትልቅ የሀገራችን መምህር ስሙ ወልደ ህይወት የተባለ> እንደፃፈልን እንድንረዳም ያስጠነቅቀናል፡፡ ወልደ ህይወት የመፅሐፉን ሐሳብ ከማስፈሩ በፊት እንደሚነግረን ያሰፈረልን ሐሳቦች በራሱ ምርምራ መልካም መሆኑንም ከለየ በኋላ የፃፈልን እንጂ ከሰው አፍ የሰማውንና ከሰው ትምህርት የተቀበለውን <ምንም እንደማይፅፍ> ነው፡፡

እንዲያውም በመፅሐፉ ያሰፈራቸው ሐሳቦች በብዙ ፀሎትና ምልጃ እውነትን እንዲያሳየው እግዚአብሔርን ከለመነ በኋላ የመረመረውንና <የአወቀውን> ለመሆኑ ነግሮን ከዚህ በኋላ "እውነት የመሰለኝን እጽፋለሁ ፤ ይኽን መፅሐፌን የምታነበው ወንድሜ ሆይ እኔም እንዳልዋሽ በሚከለክለኝ በትልቅ የእግዚአብሔር ፍርሀት እንደፃፍኩት እወቅ" በማለት ሐሳቡን በዘመኑም ሆነ በኋላ የሚመጣው ትውልድ ዘንድ ሊፈጥር የሚችለውን <ቁጣ> ማለዘቢያ የመሰለ ሐሳብ ያሰፍራል፡፡

ይሁንና ወልደ ህይወት ሐሳቡ በሰዎች ዘንድ ቁጣ ሊያስነሳበት እንደሚችል ደሞ ያጣው አይመስልም፡ ፡ ወረድ ብሎ ፡-"ነገር ግን የሰው መፍራት የለብኝም ፤ የፊታቸውንም ምንም አላፍርም፡፡ ከንቱና ሐሰትን ከሚያስተምሩና ከሚፅፉም ጋር በማናቸውም ስራ አልተባበርም፡፡ እውነትን አንተ ብቻህን ነህ የአወቅሀትን? ከአንተ በቀር ሁሉ አላወቃትምና ወደዋት እንጂ እኔ ብቻዬን አላወኳትም፡፡ ነገር ግን የሰውን ስድብና የግሩም ጨለማ ከሆነ ማህበራቸው መባረርን ስለፈሩ በግልፅ ማስተማርን አልደፈሩም" በማለት በአስተሳሰቡ ምክንያት አንዳች ቁጣና ውግዘት ቢደርስበት እንደማይፈራ ይነግረናል፡፡ እንዲያውም ባለመመርመራቸውም ያላወቁ በመሆናቸው የሰሙትን ብቻ አምነው የተቀበሉ "ሀይማኖተኛ ናቸው" ይለናል፡፡

ወልደ ህይወት በራሳቸው መርምረው ለደረሱበት እውነትና ዕውቀት ይልቅ የነገሯቸውን ብቻ አምነው ስለተቀበሉ ሀይማኖተኞች ሲነግረን እንዲህ ይላል ፡- "የቀሩት ሰዎች ግን ፅድቅ ሊሆን ሐሰት ሊሆን እንዳያውቁ አልመረመሩምና አላወቁም፡፡ አለ ምርመራ ከፊተኞቻቸው የሰሙትን አምነው ተቀበሉ፡ ፡እነ እርሱ የአባቶቻቸው ልጆች ናቸውና ይህ ካልሆነ በቀር ለሃይማኖታቸው ሌላ ምክንያት የላቸውም፡ ፡ ስአይአውቁትና ሰአይመረምሩትም በእርሱ አመኑ፡ ፡ ሁላቸውም እውነት ነው እያሉ ስለሃይማኖታቸው ይጋደላሉ፡፡ ነገር ግን ሁሉም የሰዎች ሃይማኖቶች እርስ በእርሳቸው ይከራከራሉእውነተኞች ሊሆኑ አይቻልም፡ ፡ ሐሰት ብዙ ሲሆን እውነትን ብቻዋ አንዲት ናትና ሁላቸው ግን ሐሰተኞች ሊሆኑ ይህ ይችልበታል" በማለት በሰው ካተረፈው እምነትና ሀይማኖት ልባችንን አንስተን የጥበብና የዕውነት ሁሉ መገኛ ወደ ሆነው ወደ እግዚአብሔር እንድንመለከት ይጠይቀናል፡፡

እንግዲህ ወልደ ህይወት ይኽ አስተሳሰቡ ከመነሻቸው የሀይማኖተኞችን ቁጣ እንደሚያስከትል ያወቀ ይመስላል፡ ፡ ይሁንና ድፍረትን ለራሱና ለተከታዮቹ እንዲህ ይለግሳል፡- "ወዳጄ ሆይ ዓዋቂ አድርጎ ወደ ፈጠረህ ፍፁም ህላዌ ህሊናህን አንሳ፡፡ በልቦናህም ዓይን ወደ እርሱ ተመልከት፡፡ ፈጣሪህ ወደ የአሚኣሳይህ የብርሀን አእምሮ አስተውል ፤ የአሚሰድብህን ቃላቸውን አትስማ ፤ እነርሳቸውም ፈጣሪን አላወቁትምና በእነእርሳቸውም ዘንድ ጥበብ የለም፡፡"

ወልደ ህይወት ከቀደሙት አስተሳሰብና እምነት ማፈንገጥ ብቻ ሳይሆን ወደ ፊት የምንማርና የምንሰማውም ቢሆን መርምረን መቀበል እንዳለብን ሲያሳስበን እንዲህ ይላል ፡- " አንተግን የአስተማሩህን ሁሉን ራስህ ሳትመረምረውና እውነትም ከሐሰት ሳትለይ በቀር ሰዎች የአስተማሩህን ምንም አትመን፡፡ ሰዎች ሊዋሹ ይችላሉና ፤ እውነት ወይም ሐሰት ቢያስተምሩህም አታውቅም፡፡ እንዲሁም ሳትመረምራቸውና እውነት ሁነው ሳታገኛቸው፤ በመፅሐፍት የተፃፈውን አትመን፡ ፡ መፃሕፍትን ከመረመርሃቸው እግዚአብሔር እውነት እንድንፈልግበት ከሰጠን ከልቦናችን ጋር የማይስማማ ክፉ ጥበብ ታገኝባቸዋለህ፡፡"

ወልደ ህይወት የደረሰበትን እውነት ከመንገሩ በፊት ይኽን ያህል ማስጠንቀቁ ያለምክንያት የሆነ ድካም አይመስለንም፡፡ ብዙዎቹ ዕውቀትን ሳይመረምሩ በሰሙት ነገር ብቻ ከመወሰዳቸው የተነሳ በስንፍና ጨለማ ሲዳክሩ ተመለከትሁ በማለቱ እንጂ፡፡ እናም እውነትና ሐሰትን ለይቶ ለማሳወቅና የእግዚአብሔርን ስራ ለማመን አስቀድሞ እሱ በሰጠህ ህሊና ትመረምር ዘንድ የግድ ይሆናል፡፡ "መመርመር ወደ ጥበብ የምንገባበት በር ነው" የሚለን ወልደ ህይወት " እንግዲያስ ሰዎች የሚያስተምሩንና በመፃህፍትም የተፃፈውን ሁሉ ልንመረምረው ይገባል" በማለት እሱ ህሊናዊ ምርመራ ደረስኩበት ወደሚለው የመጀመሪያው ርዕስ ይዞን ይገባል፡፡ ወልደ ህይወት አስቀድሞ የሚያነሳልን "የፍጥረት ምርመራ" በማለት ያስቀመጠልንን ሐሳብ በመፈተሽ ይሆናልና ወደዚያው እንዝለቅ፡፡

ለወልደ ህይወት የሀይማኖት ፤ ጥበብና የእውነት መሰረት እግዚአብሔር ነው፡፡ ሁሉ በእሱ እንዳለና እንደሚኖር በቅድሚያ መሰረት ማስያዝ ተገቢ መሆኑን አስቀምጦ በእሱም ማመን <መምህራን ሰዎችና የሁሉ አገር መፃህፍት> እንደሚስማሙ ልናውቅ ይገባል ይለናል፡፡ እኛም በእሱ እናምን ዘንድ የሚያስገድደን አንድ እውነት ቢኖር ዛሬ የአለን ትናንት ያልነበረንና ነገ የምንጠፋ ፍጡራን መሆናችንን ከመረዳት ላይ ሲሆን ይኸን እውነት ከተገነዘብን አለፈጣሪ ፍጡር መሆን እንደማይቻል ማሰብ አያቅተንም ባይ ነው፡፡ እንግዲህ ፍጥረት ሁሉ ከአንድ ፈጣሪ የወጣ መሆኑን መቀበል ከቻልን ሁሉን በትልቅ ጥበብ በፈጠረ በእሱ ዘንድ ስህተት አለመኖሩንም ማወቅ ሌላው ጥበብ መሆኑን ይነግረናል፡፡ ሁሉን በተወሰነለትና በሚገዛበት መንገድ ፈጥሮ እንደመራው የማይረዱ ሰዎች አሉ ፡- " ሁልጊዜ ይህና ይህ መልካም ነው ፤ ይህ ግን በአይፈጠር በተሻለ የሚሉ ዕብዶችን አትስማቸው" በማለት ስለ እነሱም ከአስጠነቀቀን በኋላ ፡-"እግዚአብሔር የሰራው ሁሉ በሰራው መንገድ እጅግ መልካም ነው" በማለት ለእኛ እይታ የማይጠይቅም መስሎ የሚታየን የፍጥረት ክፍል ለሌላዕ በጎና የሚጠቅም መሆኑን እንድንረዳ ይመክረናል፡፡

በወልደ ህይወት አስተሳሰብ ፈጣሪ በምድር ላይ የፈጠረው ነገር ሁሉ ለሰው ጥቅም የተፈጠረ ነው፡፡ ለእኛ ጥፉዎች የሚመስሉን ሁሉ ከእኛ በኋላ ጥቅማቸው እንደተገኘ የሚነግረን ወልደ ህይወት ፡-" እንዲህ ሁሉ ለሰው ጥቅም ተፈጠረ፡፡ ወይም በይህ ዓለም ሃዳሪ ለሆነው ከፍጥረት ሁሉ የእሚልቅ ለሰው ማገልገያው ሊሆን ተፈጠረ፡፡ በይህ ዓለም ከአልለው ፍጥረት ሁሉ ሰው ከፍ የአለ ነውና ፤ በልቦናውም ወደ ፈጣሪው ምሳሌ ይበርባል፡፡ በይህ ዓለም ሁሉ የኣለውም ለሰው ማደሪያና ማሳመሪው ምሳሌይቀርባል፡፡ በይህ ዓለም ሁሉ የኣለውም ለሰው ማደሪያና ማሳመሪያ እንዲሆን ተፈጠረ" በማለት የሰው ልጅ ከፍጥረት ሁሉ የላቀ ፍጡርና የፍጥረት ገዢ ተደርጎ በእግዚአብሔር መሰየሙን ቀዳሚው ዕውቀት አድርጎ ያስቀምጣል፡፡

ምንም እንኳን ሰው የፍጥረት ሁሉ ገዢና አዋቂ ቢሆንም ሁሉን የሚያስብና የሚያውቀው በነፍሱ ጥልቀት እንጂ በስጋዊ ባህሪዩ አለመሆን ወልደ ህይወት ያስቀምጣል፡ ፡ የሰው ልጅ ስጋዊ ባህርዩ መሬት ነውና ተፍሱ ከእርሱ በወጣች ጊዜ "እንደ ደረቅ ጭላንፎ ይወድቃል" ይለናል፡ ፡ "መንፈሳዊትና ተነጋሪት ነፍስ" የሚላት ወልደ ህይወት በስጋችን ውስጥ ተመሽጋ ሁሉን እንድናውቅና እንድናስብ ብታደርገንም ስለምንፈሳዊያውን ፍጥረቶች ግን ለማወቅ አታስችለንም በማለት እንደሚከተለው ያስቀምጣል ፡- "ስለ መንፈሳዊያን ፍጥረትቶች ግን ከሰው ነፍስ የእሚልቁ ሌሎች መናፍስት እንደ አልሉ እጠረጥርአለ፡ ፡ እነ እርሳቸውም መላዕክትና አጋንንት ናቸው፡፡ ሰዎች ሁላቸው መኖራቸውን አምነዋልና ፤ በእግዚአብሔር ፍጥረታትም መኖራቸው ያምራል፡፡ ነገር ግን ለእኛ ስለ እምአይታዩን በይህ እምነት ላይ ልቦናችን ዝም ይላል፡፡ እርግጠኛ ንግግርአቸው ልንአውቀው አንችልምና ስለ እነ እርሳቸው ልቦናችን ምንም አይኣረጋግጥልንም፡፡ ነገር ግን ለእኛ እርግጠኛ ከሰው ነፍስ የእሚአንሱ እንደ አልሉ እነርሳቸውም የእንስሳና አራዊት ነፍሳት ናቸው፡፡"

እዘህ ላይ ወልደ ህይወት እንደ መምህሩ ዘርአያዕቆብ ከዘመኑ የዘለማድ አስተሳሰብ አፈንጋጭ ሀሳቡን ቀስ ብሎ መሰረት ሲያበጅለት እናያለን፡፡ መላዕክትና አጋንንት በእግዚአብሔር ዘንድ ሊኖሩ ይችላሉ ፤ ነገር ግን እኛ ባለማየታችን ከፈጠረን ፈጣሪ በቀር ስለ እነሱ መኖር መናገር አንችልም ባይ ነው፡፡ ስለመኖራቸው ማረጋገጥ የማንችለውን ነገር እንዳሉ መቀበል ደግሞ ስንፍና መሆኑን ወልደ ህይወት አስቀምጦ እንስሳና አራዊትም ቢሆን በሰው ቋንቋ የሚነጋገሩ አይደሉምና "በህሊናቸው ስፋት የፈጠራቸው እንዳለና እንደሌለ የሚያውቁ አይመስሉኝም" በማለት የእነሱም ነፍስ ከሰውእንደሚለይ አስገንዝቦ የሰው ልጅ ከፍጥረት ሁሉ ታላቅ የመሆኑን እውነት አስቀድመን እንድንይዝ በማስገንዘብ ሐሳቡን መተንተን ይቀጥላል፡፡

የእንስሳትና የአራዊት ነፍስ ከሰው ሁሉ እንደምትለይ ወልደ ህይወት ሲነገረን የእሱ ህይወት ደግሞ "በአንድ ቦታ ተተክለው ተወልደው አድገው የሚሞቱ እንጂ የማይንቀሳቀሱ ከአትክልትና ከአዝርዕት ህይወት የእንስሳና የአራዊት ተፈጥሮነት ከፍ እንደሚል እንዲሁ የሰው ነፍስ ከእንስሳ ነፍስ ከፍ ይላል" በማለት በተፈጥሮ ደረጃ የሰው ልጅ ከሁሉ የላቀ ስፍራ እንዳለው ያስገነዝባል፡፡ በመሆኑም የሰው ነፍስ ወደ ፈጣሪ በሁሉ ነገሯ በእጅጉ የቀረበች በመሆኗ "የመጀመሪያውን ማዕረግ" እንደተሾመች እንድረዳና በዚህ ማዕረጓ ምክንያት ሟች እንዳልሆነች እንረዳችኋለን ይለናል፡፡ የሰው ነፍስ የማትሞት ስትሆን የእንስሳትና የአራዊት ነፍስ ግን ይሙት ወይም አይሙት አላውቅም የሚለው ወልደ ህይወት ይኸም በመሆኑ "የነፍስ ዕውቀትዋ ህላዌዋ ነው ፤ የነፍስ ዕውቀትም ከእግዚአብሔር ከፈጣሪ የወጣ የብርሀን ጮራ ነው ፤ ወደ እርሱ ተመልሶ ይገባል እንጂ አይጠፋም ፤ ከቶም ሊጠፋ አይችልም" በማለት የሰውን ነፍስ ዘላለማዊነት አለጥርጣሬ እናምን ዘንድ እንደሚገባ ይመክራል፡፡

"ስለ ዚህም የዘለዓለምን ህይወት የነባቢት ነፍስ አስፈላጊዋ ነው፡፡ አለ ይህ ግን የሰው ህላዌ ሁሉ ምትህትና ከንቱ ይሆናል፡፡ እግዚአብሔርም በሰው ፍጥረት ጠቢብ ሳይሆን አላጋጭ በሆነ" በማለት ወልደ ህይወት የሰውን ነፍስ ዘላለማዊነት ከፈጣሪው ማንነት ጋር ያቆራኘውና ይህንንም ማሰቡና ማመኑ በራሱ ምድራዊ ኑሮአችንን እንደሚያጣፍጥ እንገንዘብ ይለናል፡፡ "እንግዲህ ነፍሳችን ሟች እንደ አይደለች አለጥርጣሬ ልናምን ይገባናል፡፡ ከፈጣሪዋ ጭን የበረረች ሁና እንደወጣች እንዳይሆን ወደ እርሱ ትገባለች፡፡ እንዲሁ እንደሆነም ልቦናችን ያረጋግጥልናል፡፡ ይህም ትምህርት ሐሳባችንን ያስደስታል ፤ በእውነትነና ለመልካም ስራ ሁሉ መሰረት ይሆነናል" በማለት ወልደ ህይወት በፍጥረት ምርመራ ርዕስ የሰውን ልጅ ነፍስ ዘላለማዊነት መሰረት አስይዞ ይጠናቀቃል፡፡

እንግዲህ በወልደ ህይወት ምርመራ እንዲህ ከፍ ያለ ማዕረግና ስፍራ ያገኘችው የሰው ነፍስ የዕውቀት ሁሉ መውጫ መሆኗን በእሱ ሐሳብ ከጨበጥን በዚህች ነፍስ ሊመረመር የሚገባውስ እውነት ምን ይሆን? ብለን መጠየቃችን አይቀርም፡፡ እንደ እሱ አስተሳሰብ ፈጣሪ እውነትን እናውቅባት ዘንድ በፈጠረልን ነፍስ አስቀድመን ልናውቅ የሚገባን " እምነትን" ነው ይለናል፡፡ ይህን የአስተሳሰብ ታላቅ መገለጫና አያሌ የእምነት ሰዎችን በየትውልዱ ሲያስቆጣ የቆየውን "የእምነት መመራመር" ጉዳይ በቀጣይ ሳምንት ስንገናኝ እንቀጥላለን ፡፡ ቸር ሰንብቱልኝ፡፡

**አመሰግናለሁ**

**ማጣቀሻ ፡- ጥበብ ከጲላጦስ ቁ.2**

## የግልፅ ጨረታ ማስታወቂያ

በድሬዳዋ አስተዳደር የድልጮራ ሆስፒታል ለሆስፒታሉ አገልግሎት የሚውል ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን እቃዎች ማለትም የተለያዩ መጠንና ከለር ያላቸው የቆሻሻ ቅርጫት west bin different size and color በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ስለፈለገ ህጋዊና ብቁ ተወዳደራሪዎች አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡

በዚህ መሰረት በጨረታው ላይ ለመሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች

1. ተጫራቾች በዘርፉ ህጋዊ ንግድ ፍቃድ ያላቸውና የ2016ዓ/ም ግብር የከፈሉ፡ በተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆኑ እና ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ መሆን አለባቸው ፡፡
2. በመንግስት ግዥ አቅራቢ የሆኑ እና ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡
3. ተጫራቾች የታክስ መለያ ቁጥር (Tin no) ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል፡፡
4. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን ይህ ማስታወቂያ በድሬ ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ዘወትር በስራ ሰዓት ለ15 ተከታታይ የስራ ቀናት የማይመስ ብር 200.00 (ሁለት መቶ) እያንዳንዱ ሎት በመክፈል በድልጮራ ሆስፒታል ቢሮ ቁጥር A/02በማቅረብ ሰነዱን መግዛት ይችላሉ፡፡
5. መስፈርቱን የሚያሟሉ ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበርያ የሚሆን ብር 10,000.00 (አስር ሺ ብር) በባንክ በተመሰከረለት ቼክ ወይም (CPO) ከጨረታው ኦርጅናል ሰነድ ጋር አያይዘው ማቅረብ አለባቸው፡፡
6. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ በማድረግ ለዚህ ብሎ በተዘጋው የጨረታ መቀበያ ሳጥን ማስገባት ይኖርባቸዋል ፡፡
7. የጨረታ ሰነዱ የሚከፈትበት ቀን ይህ ጨረታ በድሬ ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ15 የስራ ቀናት ከቆየ በኃላ በ16ኛው ቀን ጠዋት 4፡00 ሠዓት ተዘግቶ ከቀኑ 4፡30 ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በሆስፒታሉ ግዥ ፋ/ን/አስዳይሬክትሬት ቢሮ ቁጥር A/02 ይከፈታል፡፡
8. የጨረታው አሸናፊ በፅሁፍ እንደተገለፀለት አስፈላጊው የጨረታ ውል ማስከበርያ በማስያዝ ከሆስፒታሉ ጋር ውል መፈረም አለበት፡፡ ይህ ባይፈፀም የጨረታ አሸናፊነቱን በመሰረዝ ለጨረታ ማስከበርያ ያስያዘው ገንዘብ ለመንግስት ገቢ ይሆናል፡፡
9. ተጫራቾች በሰነዳቸው ላይ ስማቸውን፣ ሙሉ አድራሻቸውን እና ፊርማቸውን እንዲሁም የተሟላ ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው፡፡
10. ሆስፒታሉ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው፡፡

**አድራሻ፡- በድሬዳዋ አስተዳደር የድል ጮራ ሆስፒታል**

**ስልክ ቁጥር 0982540408/0972351303/02-521115693፡**

**ፖስታ ሳጥን ቁጥር 177**

## የግልፅ ጨረታ ማስታወቂያ

በድሬዳዋ አስተዳደር የድልጮራ ሆስፒታል ለሆስፒታሉ አገልግሎት የሚውል ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን እቃዎች ማለትም printer, Desktop Computer, laptop & USP በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ስለፈለገ ህጋዊና ብቁ ተወዳዳሪዎችን አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡

በዚህ መሰረት በጨረታው ላይ ለመሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች

1. ተጫራቾች በዘርፉ ህጋዊ ንግድ ፍቃድ ያላቸውና የ2016ዓ/ም ግብር የከፈሉ፡ በተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆኑ እና ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ መሆን አለባቸው ፡፡
2. በመንግስት ግዥ አቅራቢ የሆኑ እና ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡
3. ተጫራቾች የታክስ መለያ ቁጥር (Tin no) ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል፡፡
4. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን ይህ ማስታወቂያ በድሬ ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ዘወትር በስራ ሰዓት ለ15 ተከታታይ የስራ ቀናት የማይመለስ ብር 600.00 (ስድስት መቶ ብር) እያንዳንዱ ሎት በመክፈል በድልጮራ ሆስፒታል ቢሮ ቁጥር A/02በማቅረብ ሰነዱን መግዛት ይችላሉ፡፡
5. መስፈርቱን የሚያሟሉ ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበርያ የሚሆን ብር 50,000.00 (ሃምሳ ሺ ብር) በባንክ በተመሰከረለት ቼክ ወይም (CPO) ከጨረታው ኦርጅናል ሰነድ ጋር አያይዘው ማቅረብ አለባቸው፡
6. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ በማድረግ ለዚህ ብሎ በተዘጋጀው የጨረታ መቀበያ ሳጥን ማስገባት ይኖርባቸዋል ፡፡
7. የጨረታ ሰነዱ የሚከፈትበት ቀን ይህ ጨረታ በድሬ ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ15 የስራ ቀናት ከቆየ በኃላ በ16ኛው ቀን ጠዋት 4፡00 ሠዓት ተዘግቶ ከቀኑ 4፡30 ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በሆስፒታሉ ግዥ ፋ/ን/አስዳይሬክቶሬት ቢሮ ቁጥር A/02 ይከፈታል፡፡
8. የጨረታው አሸናፊ በፅሁፍ እንደተገለፀለት አስፈላጊው የጨረታ ውል ማስከበርያ በማስያዝ ከሆስፒታሉ ጋር ውል መፈረም አለበት፡፡ ይህ ባይፈፀም የጨረታ አሸናፊነቱን በመሰረዝ ለጨረታ ማስበርያ ያስያዘው ገንዘብ ለመንግስት ገቢ ይሆናል፡፡፡፡
9. ተጫራቾች በሰነዳቸው ላይ ስማቸውን፣ ሙሉ አድራሻቸውን እና ፊርማቸውን እንዲሁም የተሟላ ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው፡፡
10. ሆስፒታሉ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው፡፡

**አድራሻ፡- በድሬዳዋ አስተዳደር የድል ጮራ ሆስፒታል**

**ስልክ ቁጥር 0982540408/0972351303/02-521115693፡**

**ፖስታ ሳጥን ቁጥር 177**

## በድጋሚ የወጣ የጨረታ ማስታወቂያ


የድሬዳዋ አስተዳደር ፖሊስ ኮምሽን ለ2016 ዓ.ም በጀት ዓመት በስሩ ለሚገኘው የእግር ኳስ ቡድን እና ብስክሌት ስፖርት ቡድን የተለያዩ የስፖርት ትጥቅ ግዥ በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለማስመገብ ይፈልጋል፡፡

ስለዚህ በጨረታ ለመሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች፣

1. የጨረታ ሠነድ የማይመለስ ብር 300/ሶስት መቶ ብር/ በመክፈል ለ15 ተከታታይቀናት በድሬዳዋ አስተዳደር ፖሊስ ኮሚሽን ፋይናንስና ግዥ ዳይሬክቶሬት የሥራ ሒደት ቢሮ ቁጥር 16 በመቅረብ መግዛት ይችላሉ፡፡
2. ተጫራቾች የዘመኑ የታደሰ ንግድ ፈቃድ ያላቸው፣ የዘመኑን ግብር ከፋይ የከፈሉበትን ማስረጃ ማቅረብ ፣ተጨማሪ እሴት ታክስ፤የአቅራቢነት ምስክር ወረቀት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
3. ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና የሚሆንና የጨረታው ውጤት እንደታወቀ የሚመለስ የሚጫረቱበትን እቃ ዋጋ 2% CPO/ወይም በጥሬ ገንዘብ ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡
4. በተዘጋጀው የጨረታ ሠነድ ላይ ዋጋ ሞልቶ ማቅረብ ተመራጭነት አለው፡፡
5. የዋጋ ማቅረቢያ ሰነድ ኦርጅናልና ኮፒ በማለት ለየብቻ በማሸግ በአንድ ኤንቨሎፕ ውስጥ በማድረግ በጨረታ ሣጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
6. የጨረታ ሰነድ የካቲት 13 ቀን እስከ የካቲት 27/2016 ዓ.ም. ከ11:00 ሰዓት በድሬዳዋ ፖሊስ ኮሚሽን በፋይናንስና ግዢ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ቢሮ ቁጥር 16 ቀርበው መግዛት ይችላሉ፡፡
7. ጨረታው የሚከፈተው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት የካቲት 29/2016 ዓ.ም. ከጠዋቱ 3.00 ሣጥኑ ታሽጎ 3.30 ሠዓት ይከፈታል፡፡
8. ፖሊስ ኮሚሽኑ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

ተጨማሪ ማብራሪያ በስልክ ቁጥር 0251-11-74-55/0251-11-37-43 በመደወል መረጃ ማግኘት ይችላሉ፡፡ ፖ.ሣ. ቁጥር 1453

**የድሬዳዋ አስተዳደር ፖሊስ ኮሚሽን**



## Invitation to Bid

Place and Date: ***Dire Dawa, January, 2024***

Procurement Reference Number: ***DDA/K02AO/PC-001/2016***

1. The ***Dire Dawa Administration Kebele 02 Administration Office*** having legal address at:

| | |
|---|---|
| Street Address: | Seyido taxi station street |
| Town/City: | Dire Dawa |

2. The ***Dire Dawa Administration Kebele 02 Administration Office*** now invites sealed bids from eligible and qualified bidders for: ***Construction of Ditch Work (Location: Bargele, Kebele 02)***.
3. Intended Completion Date for the whole of the Works shall be ***150 calendar days***.
4. Bidding will be conducted through **National Competitive Bidding** procedure contained in public proclamation of FDRE and is open to all Eligible bidders.
5. Interested eligible bidders may obtain further information from ***Dire Dawa Administration Kebele 02 Administration Office*** and inspect the bidding documents at the address given below from 7:30AM – 12:00 PM & 2:00 – 5:30 PM working hours.
6. Qualifications requirements include: Contractors of category ***GC/BC-7 & above*** with license valid for the year ***2016E.C***. ***Work Experience is Required***
7. A complete set of Bidding Documents in English may be purchased by interested bidders on the submission of a written Application to the address below and upon payment of a non-refundable fee of ***ETB 500*** in ***Cash***.
8. Bidders shall submit their Bids in **two envelopes**, the first envelop labeled as "Technical Proposal and Bid Security" and the second envelope "Financial Proposal", separate sealed and the two envelopes sealed in on other outer envelope.
9. Evaluation is to be carried out in two stages, Technical Proposal first and Financial Proposal of qualified Bidders next.
10. Bids must be delivered to the address below at or *before* ***9:00 AM morning time*** on the ***22nd*** Date from the Date of Announcement. Late bids will be rejected.
11. Bids Will Be Opened In The Presence Of Bidder's Representatives Who Choose To Attend at The Same Date of Submission at ***9:30 AM morning time***
12. All bids must be accompanied by a Bid Security of ***ETB 100,000.00 (One Hundred Thousand Ethiopian Birr) in the form of Cash, an Unconditional Bank Guarantee, or CPO***. The Bid Security shall be valid for 28 days beyond the validity of the Bid.
13. The public body reserves the right to reject any bid and to annul the bidding process and reject all bids at any time prior to contract award, without thereby incurring any liability to Bidders.
14. The address referred to above is:

| | |
|---|---|
| Public Body: | Dire Dawa Administration Kebele 02 Administration Office |
| Street Address: | Seyido taxi station street |
| Town/City: | Dire Dawa |

## የጨረታ ማስታወቂያ

የድሬዳዋ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የግንባታ ቁሳቁሶች ግዥ ለመፈጸም አቅራቢ

ድርጅቶችን በጨረታው እንዲሳተፉ ይጋብዛል፡፡

ስለዚህም፡-

- በዘርፉ ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ያላቸው የዘመኑን ግብር የከፈለና ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣
- የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ባዘጋጀው የእቃና የአገልግሎት አቅራቢነት ዝርዝር የተመዘገቡና ለዚህም የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችል፣
- የግብር መክፈል ግዴታቸውን የተወጡ መሆኑን የሚያረጋግጥ በግብር ሰብሳቢነት ባለ ስልጣን የተሰጠ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣
- በተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢነት ሰርተፍኬት ማቅረብ የሚችል፣
- ታክስ ክሪናንስ ማቅረብ የሚችል
- ተጫራቾች ጨረታውን ዝርዝር የያዘ ሰነድ የማይመለስ ብር 200.00 (ሁለት መቶ ብር) በመክፈል ይህ የጨረታ ማስታወቂያ በድሬ ጋዜጣ ከወጣበት የመጀመሪያው ቀን ጀምሮ ለተከታታይ 21 ቀናት ዘወትር በስራ ሰዓት በድሬዳዋ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የግዥ ፋይናንስ ንብረት አስተዳደር ደጋፊ የስራ ሂደት 1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 103 በመቅረብ መግዛት የሚችል፣
- ተጫራቾች ጨረታ ማስከበሪያ 20/ሃያ ሺህ/በባንክ በተመሰከረለት ቼክ (CPO) ከጨረታ ሰነዱ ጋር አያይዞ ማቅረብ የሚችል፣
- ተጫራቾች በጨረታ ያሸነፏቸውን እቃዎች በራሳቸው ትራንስፖርት በ10 ቀን ውስጥ ቢሮ ድረስ ገቢ ማድረግ የሚችል፣
- ተጫራቾች የሚጫረቱበትን ዋጋ በሰም በታሸገ ኢንቨሎፕ በማድረግ ማስታወቂያው በድሬ ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 21 ተከታታይ ቀናት በስራ ሰዓት ከላይ በተጠቀሰው ቢሮ በመቅረብ የሚወዳደሩበትን ዋጋ በመሙላት የጨረታ ሰነዱን በ22ኛው ቀን ከጠዋቱ 1፡30 እስከ 4 ሰዓት ለጨረታው በተዘጋቸው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡፡ ጨረታው በ22ኛው ቀን 4፡00 ሰዓት ይታሸጋል በዛው እለት ከጠዋቱ በ4፡30 ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በግልጽ ይከፈታል፡፡ ይህ ቀን ግን የስራ ቀን ካልሆነ በቀጣይ የስራ ቀን ይከፈታል፡፡

ማሳሰቢያ፡- ቢሮው የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለተጨማሪ መረጃ፡- በስልክ ቁጥር 02511128435 መደወል ይችላሉ፡፡**

**የድሬዳዋ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የግዥ ፋይ/ንብ/አስ/ደጋፊ የስራ ሂደት**

## የጨረታ ማስታወቂያ

የድሬዳዋ አስተዳደር ፖሊስ ኮምሽን ለ2016 ዓ.ም በጀት ዓመት በስሩ የሚገኙትን መኪናዎች የጋራዥ ጥገና አገልግሎት በጨረታ አወዳድሮ ለአንድ አመት ለማስጠገን ስለሚፈልግ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የምታሟሉ ተጫራቾች በጨረታው እንድትሳተፉ ይጋብዛል፡፡

1. የጨረታ ሠነድ የማይመለስ ብር 300/ሶስት መቶ ብር/ በመክፈል ለ15 ተከታታይ ቀናት በድሬዳዋ ፖሊስ ኮሚሽን ፋይናንስና ግዥ ዳይሬክቶሬት የሥራ ሒደት ቢሮ ቁጥር 16 በመቅረብ መግዛት ይችላሉ፡፡
2. ተጫራቾች የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ፤የዘመኑ የታደሰ ንግድ ስራ ፈቃድ ያላቸው፣ የዘመኑን ግብር ከፋይ የከፈሉበትን ማስረጃ ማቅረብ ፣ተጨማሪ እሴት ታክስ፤የአቅራቢነት ምስክር ወረቀት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
3. ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና የሚሆንና የጨረታው ውጤት እንደታወቀ የሚመለስ የሚጫረቱበትን እቃ ዋጋ 2% CPO/ወይም በጥሬ ገንዘብ ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡
4. በተዘጋጀው የጨረታ ሠነድ ላይ ዋጋ ሞልቶ ማቅረብ ተመራጭነት አለው፡፡
5. የዋጋ ማቅረቢያ ሰነድ ኦርጅናልና ኮፒ በማለት ለየብቻ በፖስታ በማሸግ በአንድ ኤንቨሎፕ ውስጥ በማድረግ በጨረታ ሣጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
6. የጨረታ ሰነድ የካቲት 13 ቀን እስከ የካቲት 26/2016 ዓ.ም. ከ11:00 ሰዓት በድሬዳዋ ፖሊስ ኮሚሽን በፋይናንስና ግዢ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ቢሮ ቁጥር 16 ቀርበው መግዛት ይችላሉ፡፡
7. ጨረታው የሚከፈተው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት የካቲት 28 ቀን 2016 ዓ.ም. ከጠዋቱ 3.00 ሣጥኑ ታሽጎ 3.30 ሠዓት ይከፈታል፡፡
8. ፖሊስ ኮሚሽኑ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

ለተጨማሪ ማብራሪያ በስልክ ቁጥር 0251-11-74-55/0251-11-37-43 በመደወል መረጃ ማግኘት ይችላሉ፡፡ ፖ.ሣ.ቁጥር 1453

**የድሬዳዋ ፖሊስ ኮሚሽን**

## ማስታወቂያ

በከሳሽ አቶ ሁሴን መሀመድ እስማኤል እና በተከሳሾች 1. አቶ ሱሌይማን ሆሽ አስዬ 2. አቶ ቬባን ዲሔዬ ጃማ መካከል ስላለው የፍትሐብሄር ክርክር ጉዳይ ከሳሽ ያቀረቡትን ክስና ማስረጃ ከፍ/ቤቱ ሬጅስትራር በኩል ቀርበው በመውሰድ ለክሱ ያላቸውን መልስ በፁሑፍ በሶፍት ኮፒ ጭምር ለየካቲት 22 ቀን 2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት አዘጋጅተው በሬጅስትራር ጽ/ቤት በኩል እንዲያያይዙ እና ለቃል ክርክር ተዘጋጅተው ለየካቲት 29 ቀን 2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እንዲቀርቡ የድ/ዳ አስ/የመ/ደረጃ ፍ/ቤት 2ኛ ፍትሐብሄር ችሎት አዟል፡፡

**የድ/ዳ አስ/የመ/ደረጃ ፍ/ቤት**

## ማስታወቂያ

1. የፈርኒቸርግዥ

ከላይ በቁጥር 1 ላይ የተጠቀሰው ይህ ማስታወቂያ በድሬ ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጨረታውን ሰነድ የማይመለስ ብር 300.00 (ሶስት መቶ ብር) በመክፈል ከድሬዳዋ ጤና ጥበቃ ቢሮ ግዥና ፋይናንስ ክፍልበመግዛት የመወዳደሪያ ዋጋ የያዘውን ሰነድ በሰም በታሸገ ኢንቨሎፕ በማድረግ ጨረታው ከወጣበት ቀን ጀምሮ ከ15 ቀናት በኃላ (በ16ኛው የስራ ቀን) ከጠዋቱ 3፡30 ድረስ ለዚህ ተግባር በተዘጋጀውና በግዥ፣ ፋይናንስ ንብረት አስተዳደር ዳሬክቶሬት ቢሮ ውስጥ በሚገኘው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡

በጨረታው ለመሳተፍ፡-

- የዘመኑን ግብር የተከፈለበት የታደሰ የንግድ ፍቃድ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
- ተጨማሪ እሴት ታክስ (ቫት) ተመዝጋቢ ስለመሆናቸው የሚያረጋግጥ ሰርተፍኬት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
- የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ገንዘብ (ቢድ ቦንድ) በ4ባንክ የተመሰከረለት የክፍያ ትዕዛዝ (CPO) ከሚወዳደሩበት ጠቅላላ ዋጋ ብር 5000.00 (አምስት ሺ ብር) ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡
- አንድ ተጫራች በሚያቀርበው ዋጋ ላይ ተንተርሶ ዋጋ መቀነስም ሆነ መጨመር የማይችል መሆኑን፡
- በጨረታው ለተሸነፉት ያስያዙት የጨረታ ማስመስከሪያ ገንዘብ ወድያውኑ የሚመለስላቸው ሲሆን የአሸናፊዎች ግን ከመ/ቤቱ ጋር ውል ሲፈፅሙና የውል ማስከበሪያ የጠቅላላ ዋጋውን 10% ሲያሲዙ ብቻ የሚመለስ ይሆናል፡፡
- የጨረታው አሸናፊዎች በ10ቀን ጊዜ ውስጥ ቀርበው ውል ባይፈፅሙና የውል ማስከበሪያ ባያሲዙ የጨረታ አሸናፊነታቸው ተሰርዞ ያስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ገንዘብ የሚወረስ መሆኑን፡-
- የጨረታ ሳጥኑ ጨረታው ከወጣበት ቀን ጨምሮ ከ15 ቀናት በኋላ (በ16ኛው የስራ ቀን) ከጠዋቱ በ3፡30 ይታሸጋል፡፡
- ጨረታው በ16ኛ የስራ ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በመ/ቤቱ አዳራሽ የሚከፈት መሆኑን፡-
- መ/ቤቱ የተሻለ ዘዴካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
- ስለጨረታው ተጨማሪ ማብራሪያ ቢያስፈልግ በስ/ቁጥሮች 09-93-67-21-57/0929250471 ደውሎ መጠየቅ የሚቻል መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**የድሬዳዋ አስተዳደር ጤና ጥበቃ ቢሮ**

## በድጋሜ የወጣ የግዢ ጨረታ ማስታወቂያ

የድሬዳዋ አስተዳደር ሥራ፣ ክሎትና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ለ2016 ዓ.ም የአይ.ሲ.ቲ የመሠረተ ልማት ዕቃዎችን በጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡ ስለዚህበ ጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች ሁሉ ከዚህ በታች የተመለከቱትን

መስፈርቶች በሟሟላት መወዳደር ይችላሉ፡፡

1. ተጫራቾች የቫት ተመዝጋቢ፣ በሥራው መስክ ህጋዊና የታደሠ የንግድ ፍቃድ ያላቸው፣ የዘመኑን ግብር የከፈሉና የአቅራቢነት የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ፣
2. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ለእያንዳዱ ሰነድ 5000.00 (አምስት ሺህ ብር) በባንክ በተመሠከረ ቼክ (CPO) ከጨረታ ሠነዱ ጋር አያይዘው ማቅረብ አለባቸው፣
3. ተጫራቾች የተዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ የማይመለስ ብር 500 (አምስት መቶ ብር) በመክፈል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ድሬዳዋ አስተዳደር ሥራ፣ ክህሎትና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ የግዢ፣ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ደጋፊ ዳይሬክቶሬት መግዛት ይችላሉ፡፡
4. በጨረታው አሸናፊ የሚሆኑ ተጫራቾች በጨረታ ሠነድ ላይ ለተዘረዘሩት ዕቃዎች (ለተጫረቱበት) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከእያንዳንዱ ዕቃ ናሙና ወይም Sample ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
5. ተጫራቾች ላሸነፉባቸው ዕቃዎች የጠቅላላ ዋጋ 10% በውል ማስከበሪያነት ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡
6. ተጫራቾች የጨረታ መወዳደሪያ ዋጋቸውን በገዙት የጨረታ ሠነድ ላይ ባለው ዝርዝር ሞልተው ኦርጅናልና ኮፒ በማድረግ ለዚሁ በተዘጋጀው ድሬዳዋ አስተዳደር ሥራ፣ ክህሎትና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ የጨረታ ሳጥን በድሬ ጋዜጣ ከወጣበት ቀንጀምሮ 15 ተከታታይ ቀናት ማስገባት ይችላሉ፡፡
7. የጨረታው ሳጥን የሚዘጋው በ16ኛ ቀን በዕለቱ በ 3፡30 ሠዓት ሆኖ ጨረታው የሚከፈተው በዕለቱ 4፡00 ሠዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ድሬዳዋ አስተዳደር ሥራ፣ ክህሎትና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ የግዢ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደርዳ ይሬክቶሬት ይከፈታል፡፡
8. አሸናፊ ተጫራቾች ያሸነፉባቸውን እቃዎች በ10 ቀናት ውስጥ በራሳቸው ትራንስፖርት በማጓጓዝ ቢሮው ግቢ ድረስ አምጥተው ያስረክባሉ፡፡
9. ቢሮው የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሠረዝ መብት አለው፡፡

- ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር 0251310011ወይም 0912994637 በመደወል ማብራሪያ መጠየቅ ይችላሉ፡፡ የድሬዳዋ አስተዳደር ሥራ፣ ክህሎትና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ

## ማስታወቂያ

በአመልካች ወ/ሮ ደሱ መሀመድ አህመድ እና በተጠሪ አቶ ጀማል መሀመድ አህመድ መካከል ስላለው የባልና ሚስት ክስ ጉዳይ በተመለከተ ተጠሪ መከሰሶን አውቀው አመልካች ያቀረቡትን ክስና ማስረጃ ከፍ/ቤቱ ሬጅስትራር ቀርበው በመውሰድ መልስዎን አዘጋጅተው በሬጅስትራር በኩል መጋቢት 2 ቀን 2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 2፡30 እንዲያቀርቡና በአስማሚ በኩል ግራ ቀኛችሁ መጋቢት 4 ቀን 2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 2፡00 ሰዓት እንድትቀርቡ ክስ ለመስማት ደግሞ መጋቢት 5 ቀን 2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት የድ/ዳ የፌ/የመ/ደረጃ ፍ/ቤት 1ኛ ቤተሰብ ችሎት አዟል፡፡

**የድ/ዳ የፌ/የመ/ደረጃ ፍ/ቤት**

# ዓውደ - ፍትህ

ረቡዕ -የካቲት / 20 / 2016 ዓ.ም ድሬ ጋዜጣ



## በድሬዳዋ አስተዳደር የሚፈፀሙ ወንጀሎችንና ህገ - ወጥ ድርጊቶችን ለመከላከል በአስተዳደራችን በተለያየ ጊዜ በተደረገ የኦፕሬሽን ስራ ህገ-ወጥ የጦር መሳሪያ በቁጥጥር መዋሉን የድሬዳዋ አስተዳደር ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ ገለፀ

የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ ከሌሎች የፀጥታ እና የአስተዳደር አካላት እንዲሁምከኅብረተሰቡ ጋር በመቀናጀት በተለያዩአካባቢዎች በተከናወኑየኦፕሬሽን ስራዎች በርካታ የተፈፀሙ ወንጀሎችን ፣ የተለያየ የወንጀል ተሳትፎካላቸው ግለሰቦች ጋር ይዞምርመራ እያጣራ ይገኛል፡፡

በድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ በወንጀል ምርመራ ዘርፍ የከባድ ውንብድና ዘረፋና የተደራጁ ወንጀሎች ዲቪዥን ኃላፊኢ/ር ቴዎድሮስ ብስራት እንደገለፁት የድሬደዋ አስተዳደርን ከወንጀል ስጋት ነፃ ለማድረግ ባሳለፍነው5 ወር ተከታታይነት ያለው አምርቂየወንጀል ምርመራ ስራ መስራት ተችሏል ብለዋል፡፡

በዚህም መሠረት ከመስከረም እስከ ጥር 2016 ዓ.ም በድሬዳዋ አስተዳደር ውስጥ በሚገኙ በተለያዩ አካባቢዎች ከኅብረተሰቡ በደረሰ ጥቆማ መሰረት እና ፖሊስ ባደረገው ኦፕሬሽን አራት ሽጉጥ፣ አንድ ታጣፊ ክላሽንኮቭ እና ሁለት መቶ አርባ ስድስት የተለያዩ ተተኳሽ ጥይቶችን ጨምሮ ስድስት ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ስር መዋላቸውን በድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ




መምሪያ በወንጀል ምርመራ ዘርፍ የከባድ ውንብድና እና ዘረፋ የተደራጁ ወንጀሎች ዲቪዥን ሀላፊ ኢ/ር ቴድሮስ ብስራት ጨምረውገልፀዋል።

እነዚህን ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ስር ለማዋል በተደረገ ኦፕሬሽን ላይ ትልቁን ሚና ለተወጡ





የድሬዳዋ አስተዳደር ነዋሪዎች ምስጋናቸውን ያቀረቡት ኢ/ር ቴዎድሮስ ብስራትየድሬደዋ አስተዳደር ሰላም አስተማማኝ እና ዘላቂ ለማድረግ ፖሊስ እየወሰደ ያለውን የተቀናጀ ስራ አጠናክሮ እንደሚቀጥል ጨምረው ተናግረዋል ።

## "በወንጀል መከላከል ስራችን በተገኙ ድሎች መዘናጋት ሳይኖር የተጀመሩ ስራዎችን አጠናክረን ማስቀጠል ይኖርብናል"

**ም/ኮሚሽነር ጉሌድ ድሪዬ**

**በድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ የወንጀል መከላከል ዘርፍ ኃላፊ**

በድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ የወንጀል መከላከል ዘርፍ የ2016 ዓ.ም የግማሽ ዓመት የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ግምገማ የዘርፉ ኃላፊ ም/ኮሚሽነር ጉሌድ ድሪዬ፣ በዘርፉ ስር የሚገኙ የሶስቱ ዳይሬክቶሬት ኃላፊዎች ፣ የዲቪዥን ኃላፊዎች እንዲሁም የሁሉም ፖሊስጣቢያ የወንጀል መከላከል እና የማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ አገልግሎት አስተባባሪዎች በተገኙበት በቢ ካፒታል ሆቴል ተካሂዷል ።

በመድረኩ ላይ በመገኘት የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት በድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ የወንጀል መከላከል ዘርፍ ኃላፊም/ኮሚሽነር ጉሌድ ድሪዬ እንደተናገሩት ባለፉት ስድስት ወራት እንደ ድሬዳዋ አስተዳደር የነዋሪዎች ሠላምና ደኅንነት በመጠበቅ እና የህግ የበላይነት ለማረጋገጥ ከአስተዳደሩ ነዋሪዎች ጋር በተቀናጀ መልኩ በተሰሩ ስራዎች የላቀ ውጤት ማስመዝገብ መቻሉን ተናግረዋል ።

ከክቡር ከንቲባ ጀምሮ መላው የአስተዳደሩ ከፍተኛ አመራሮች ለሠላም ቅድሚያ በመሥጠት በከፍተኛ ትኩረት ሲሰሩ እንደነበሩ የገለፁት ም/ኮሚሽነር ጉሌድ ድሪዬ በተገኙ ድሎች መዘናጋት ሳይኖር የተጀመሩ ስራዎችን አጠናክረን ማስቀጠል ይኖርብናል ብለዋል።

በዘርፉ ስር የሚገኙ የሶስቱ ዳይሬክቶሬት ኃላፊዎች በበኩላቸው በተቀመጠው ዕቅድ መስራት የተቋሙን




ተልዕኮ እና ርዕይ ለማሳካት ይበልጥ ከማኅበረሰቡ ጋር በመቀናጀት መስራት ይኖርብናል ብለዋል።

በመድረኩ ላይ በወንጀል መከላከል ዘርፍ ባለፉት ስድስት ወራት የተሰሩ ስራዎች በሪፖርት መልክ በኮማንደር ነጋዓለም ተሾመ በወንጀል መከላከል ዘርፍየኮምሽነር ፅ/ቤት ኃላፊ የቀረበ ሲሆን በዋንኛነት በተለይ አስከፊውን የትራፊክ አደጋን አስቀድሞ ለመከላከል የግንዛቤ ስራ ላይ ትኩረት በማድረግ ከ71ሺ. በላይ ለሚሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ ማሳደጊያ ስራ መሰራቱ የተገለፀ ሲሆን ለሽብር ጥቃት ተጋላጭ የሆኑ የመሰረተ ልማት አውታሮችና የመንግስት ተቋማት ጥበቃ ስራተኞች እና አመራሮች ስልጠና የመስጠት ተግባራት እና ሌሎች በዘርፉ የተከናወኑ ስራዎች በሪፖርቱ ተገልጿል ።

መድረኩ ላይ የሁሉም ፖሊስ ጣቢያ የወንጀል መከላከል እና የማኅበረሰብ አቀፍ ፖሊስ አገልግሎት አስተባባሪዎች የስራ ሪፖርታቸውን ያቀረቡ ሲሆን ለዘርፉ ስራ ስኬታማነት በከፍተኛ አጋርነት ሲሰሩ ለነበሩ የሌሊት ታክሲ አሽከርካሪዎች ማኅበር እና ለወጣቶች አደረጃጀት የምስጋና የምስክር ወረቀት ተበርክቶላቸዋል።

## "የድሬዳዋ ፖሊስ ለችግራችን ለሰጠን ፈጣን መፍትሔ እና የህግ የበላይነት በማረጋገጥ ላሳየን ቀና ትብብር ምስጋናችን የላቀ ነው"

**የግል ተበዳዮች**

ከአምቦ ወደ ድሬዳዋ በቆሎ ለመነገድ ሁለት ግለሰቦች ነዋሪነቱን በድሬዳዋ ከተማ ካደረገው ተከሳሽ ጋር ተነጋግረው በመተማመን ይመጣሉ ታዲያ ጥር 11 ቀን 2016 ዓ.ም በወረዳ 4ገንደቆሬአካባቢ ከሚገኝ አንድ ወፍጮ ቤት የጫኑትን በቆሎ በማራገፍ የ191 ሺ.ብር ቼክ የበቆሎ ባለቤቶች ልከውኝ ነው በማለት ከወፍጮ ቤቱ ባለቤቶች ላይ በዕምነት ያሳደሩበት ተከሳሽ ወስዶ ይሰወራል ታዲያ ከአምቦ የመጡት እንግዶች ተከሳሽን ስልክ በመደወል ገንዘቡን እንዲሰጣቸው ቢጠይቁትም ከዚህ በፊት የነበረበትን እዳ እንደከፈለ እና ገንዘቡን ሊሰጣቸው እንደማይችልተናግሮ ስልኩን በማጥፋት ይሰወራል፡፡

በሁኔታው ግራ የተጋቡት ነጋዴዎች ገንዘባቸው መበላታቸውን እና እንደማያገኙት ተስፋ በመቁረጥ ለማንኛውም በማለት ለገንደቆሬ ፖሊስ ጣቢያ ያመለክታሉ፡፡ ፖሊስም ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት ከባንክ ጋር በመነጋገር የተፃፈውን ቼክ እንዲታገድ በማድረግ ለግል ተበዳዮች ለችግራቸው መፍቻ ያስችላቸው ዘንድ በቆሎውን ካራገፉበት ባለቤት የተወሰነ ጥሬ ብር እንዲሰጣቸው በማድረግ የተከሳሽን አድራሻ ከባንክ አካውንቱ በማፈላለግ በተለምዶ ጀርባ




እየተባለ በሚጠራው አካበቢ እንደሚኖር ማወቅ በመቻሉ ፖሊስ ባደረገው ብርቱ ክትትል ተከሳሽ ግለሰብን በቁጥጥር ስር በማዋል ለግል ተበዳዮች በአጭር ቀን ውስጥ ሙሉ ገንዘባቸውን እንዲመለስ ያደረገ ሲሆን በተከሳሽ ላይ ምርመራውን እያጣራ እንደሚገኝ የገንደቆሬ ፖሊስ ጣቢያ ምርመራ ክፍል ተወካይ ኃላፊ ዋ/ሳጅን ስንዱ ካሳሁን ገልፀዋል፡፡

ገንዘባቸውን በአጭር ቀን ውስጥ የተመለሰላቸው ከአምቦ የመጡት ሁለቱ ነጋዴዎች የድሬዳዋ ፖሊስ የህግ የበላይነት ለማረጋገጥ ትኩረት ሰጥቶ ላሳየው ቀና ትብብር የላቀ ምስጋናቸውንበጠቅላይ መምሪያው በመገኘት አቅርበዋል፡፡

## በፌዴራል ማረሚያ ቤት ኮሚሽን የድሬዳዋ ማረሚያ ቤት ማዕከል የፍሳሽ ማስወገጃ እና ማጣሪያ ግንባታ ፕሮጀክት ተጠናቆ ተመረቀ



ይሄው የፍሳሽ ማስወገጃ እና ማጣሪያ ግንባታ ከ277 ሚሊዮን 3 መቶ ሺህ ብር በላይ በሆነ በጀት መጠናቀቁም ተገልጿል ።

በዚሁ የምረቃ ፕሮግራም ላይ ተገኝተው ጉብኝት እና ንግግር ያደረጉት የኢፌዲሪ ፍትህ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዶክተር ጌዲዮን ጢሞቴዎስ እንደገለጹት ማረሚያ ቤቶች የትምህርት እና የምርት ማዕከል መሆን አለባቸው ባልነው መሰረት የድሬዳዋ ማረሚያ ማዕከል ለታራሚዎች የሚሰጡ አምራች እና የተማረ ዜጋን መፍጠሪያ ስልጠናዎች ለሌሎች ማረሚያ ማዕከላት ምሳሌ የሚሆን ነው በማለት መደሰታቸውን ገልፀው ለዛሬ ምረቃ የበቃውም ፕሮጀክት በሀገር ልጆች የተሰራ እና የልምድ ሽግግር የተደረገበት በመሆኑ ሊተኮር ይገባል ብለው ይህ ፕሮጀክት ፍሳሽን በማጣራት ከማረሚያ ቤቱ አልፎ ለአስተዳደሩ እና ለሀገር የሚኖረው ጠቀሜታ የጎላ እንደሆነ አንስተው ማረሚያ ቤቱ ከአስተዳደሩ ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሰራርን በማድነቅ ከዚህ የተሻለ ስራ ለመስራት መትጋት እንደሚገባም ተናግረዋል።

ክቡር አቶ ሀርቢ ቡህ የድሬዳዋ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ እና የንግድ ኢንዱስትሪ እና ኢንቨስትመንት ቢሮ ሀላፊ በመድረኩ ላይ ተገኝተው እንደገለፁት የድሬዳዋ ማረሚያ ቤት ማዕከል በየግዜው እያከናወነ ያለውን የለውጥ ስራዎች አድንቀው ለታራሚዎች ከህግ እርምት ባሻገር በአዕምሮ እና በሙያ አዳብረው የእርምት ግዜያቸውን አጠናቀው ወደ ማህበረሰቡ በሚቀላቀሉበት ግዜ ወንጀል ጠል አምራች ዜጋ በመፍጠር ለተሰሩ ጠንካራ ስራዎች አመስግነው መስተዳድሩ ከማረሚያ ማዕከሉ ጎን በመቆም አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርግ አስታውቀዋል ።

በዚሁ የፍሳሽ ማስወገጃ እና ማጣሪያ ግንባታ ፕሮጀክት ጋር ተያይዞ አጠቃላይ የግንባታውን ሂደት ሪፖርት ያቀረቡት የፌደራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ኮሚሽነር ጀነራል ዳመና ዳሮታ እንደገለፁት በ 2010 ዓ/ም ጅማሮውን ያደረገው እና ለዛሬው ምረቃ የበቃው ይህ ፕሮጀክት ከ277 ሚሊየን ብር በላይ በመንግሥት በጀት መሰራት መቻሉን እና የሚጣራውም ውሀ ከተቋሙ አልፎ ሌሎችንም ተጠቃሚ እንደ ሚያደርግ ተናግረው በወቅቱ ይህን ፕሮጀክት ለመስራት በሀገር ውስጥ በቂ ልምድ ስላልነበረ ከውጪ ሀገር ልምድ በመውሰድ ሀገር በቀል በሆነው የ ቲ ኤን ቲ ኮንስትራክሽን እና በፈረንሳይ ሀገር በዘርፉ ልምድ ባካበተው ኢ ሞ በተሰኘው ድርጅት ተገንብቶ ለምረቃ ለመብቃት መቻሉን ገልፀዋል ።

ለክብር እንግዶቹ ደማቅ አቀባበል በማድረግ በማረሚያ ማዕከሉ የትምህርት እና የምርት ስልጠና የሚሰጥባቸውን እና የሚመረትባቸውን ስፍራ ያስጎበኙት የድሬዳዋ ሁለገብ ማረሚያ ማዕከል ዳይሬክተር ረ/ኮሚሽነር ወንድሙ ደበላ የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር አድርገዋል ።

በዚሁ የምረቃ መርሐ ግብር ላይም የኢፌዴሪ ፍትህ ሚኒስቴር ሚንስትር ዶክተር ጌዲዮን ጢሞቴዎስ፣ ክቡር አቶ ሀርቢ ቡህ የድሬዳዋ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ እና የንግድ ኢንዱስትሪ እና ኢንቨስትመንት ቢሮ ሀላፊ ፣ ሚኒስትር ዴኤታዎች ፣የፌደራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ኮሚሽነር ጀነራል ዳመና ዳሮታ ፣ የድሬደዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ አዛዥ ክቡር ኮሚሽነር ዓለሙ መግራ፣ የድሬዳዋ ሁለገብ ማረሚያ ማዕከል ዳይሬክተር ረ/ኮሚሽነር ወንድሙ ደበላ ፣ የቢሮ ሀላፊዎች፣ የማረሚያ ቤቱ አመራር እና አባላቶች፣ የህግ ታራሚዎች ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በተገኙበት ፕሮጀክቱ በይፋ ተመርቋል ።




19ኛ ዓመት ቁጥር 864 ሳምንታዊ ዕትም ረቡዕ - የካቲት / 20 / 2016 ዓ.ም

# የድሬዳዋ ከተማ ስቴዲየም አለም አቀፍ ጨዋታን አስተናገደ

በብሩክ ደስታ

የድሬዳዋ ከተማ ስቴዲየም የፊፋ እና የካፍ መስፈርቶችን፥አለም አቀፍ ጨዋታዎችን ለማስተናገድ የሚያስችለውን ደረጃ በማሟላት የኢትዮጵያ ብሄራዊየእግር ኳስ ቡድን ከዩጋንዳ አቻው ጋር የሚያደርገውን የወዳጅነት አለም አቀፍጨዋታውን አስተናግዷል።

የድሬዳዋ ስቴዲየም ወደ ቀደሞ ክብር እና ዝናው ለመመለስ አስተዳደሩ ከፍተኛ ርብርብ በማድረግ የስቴዲየሙን የማስፋፊያ እና እድሳት ስራዎችን ሲያደርግ ቆይቶ ፤ የእግር ኳስ ሜዳው የሠው ሠራሽ የሳር ንጣፍ ሙሉ ለሙሉ ተጠናቆተመርቋል።

የድሬዳዋ ስታዲየምን እንዲታደሥና የድሬዳዋን የገነነ የቀድሞ ገጽታዋን በማደስ በኩል ከፍተኛ አሻራቸውን ያኖሩት የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ አቶ ከድር ጁሀር የድሬዳዋ ስቴዲየም አለም አቀፍ ጫወታዎችን በሚያስተናግደው መርሀ ግብር ላይ በመገኘታቸው ከፍተኛ ደስታ እንደፈጠረላቸው ተናግረዋል።

የድሬዳዋ አለም አቀፍ ስቴዲየም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ለሚያካሂዳቸው አህጉር አቀፍና አለም አቀፍ ማጣሪያ ጨዋታዎች በሜዳ እጦት ከሀገር ውጪ በግዴታ ለሚያደርጋቸው ጨዋታዎች የሚወጣውን ወጪ በማስቀረት በኩል የጎላ ሚና ይጫወታል ብለዋል።






በኢትዮጵያና በዩጋንዳ ብሔራዊ በድኖች መካከል በተካሄደው የወዳጅነት ጨዋታ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድንቢኒያም አይተን ባስቆጠረው አንድ ጎል ጨዋታውን 1ለ 0 በማሸነፍ አጠናቋል።

# የሁለተኛ ዙር የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ከ16ኛ ሳምንት እስከ 22ተኛ ሳምንት በድሬዳዋ ኢንተርናሽናል ስታዲየም ይደረጋል

የ2016 የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ ሁለተኛው ዙር ውድድር በድሬደዋ ከተማ ድሬደዋ ስታዲየም የካቲት 21/2016 ዓ.ም እንደሚጀምር መገለፁ ይታወቃል። የሁለተኛ ዙር የውድድር መርሃ ግብሩም የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን ያሉበትን ጨዋታዎች እና የኢትዮጵያ ዋንጫ ቀጣይ ጨዋታዎችን ታሳቢ በማድረግከ16ኛ እስከ 22ኛ ሳምንት በድሬደዋ ስታዲየም ፣ ከ23ኛ እስከ 27ኛ ሳምንት በሃዋሳ ዩንቨርሲቲ ስታዲየም እንዲሁም የመጨረሻዎች ሶስት ሳምንታት በአዲስ አበባ ስታዲየም የሚደረግ ይሆናል።



የ2016 የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ
ETHIOPIAN PREMIER LEAGUE 2023/24

ሳምንት 16

| ተቁ | ተጋጣሚዎች | ቀን | ሰአት |
|---|---|---|---|
| 1 | ባህርዳር ከተማ - ኢትዮጵያ መድን | ሐሙስ የካቲት 21 2016 | 10:00 |
| 2 | ድሬደዋ ከተማ - ሀምበሪቾ | ሐሙስ የካቲት 21 2016 | 01:00 |
| 3 | መቻል - ሀዲያ ሆሳዕና | አርብ የካቲት 22 2016 | 10:00 |
| 4 | ፋሲል ከነማ - ሃዋሳ ከተማ | አርብ የካቲት 22 2016 | 01:00 |
| 5 | ወልቂጤ ከተማ - ቅዱስ ጊዮርጊስ | ቅዳሜ የካቲት 23 2016 | 10:00 |
| 6 | ወላይታ ድቻ - ሻሸመኔ ከተማ | ቅዳሜ የካቲት 23 2016 | 01:00 |
| 7 | ኢትዮጵያ ቡና - ሲዳማ ቡና | እሁድ የካቲት 24 2016 | 10:00 |
| 8 | ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - አዳማ ከተማ | እሁድ የካቲት 24 2016 | 01:00 |

ሳምንት 17

| ተቁ | ተጋጣሚዎች | ቀን | ሰአት |
|---|---|---|---|
| 1 | ሃዋሳ ከተማ - ሻሸመኔ ከተማ | ሐሙስ የካቲት 28 2016 | 10:00 |
| 2 | መቻል - ባህርዳር ከተማ | ሐሙስ የካቲት 28 2016 | 01:00 |
| 3 | አዳማ ከተማ - ወላይታ ድቻ | አርብ የካቲት 29 2016 | 10:00 |
| 4 | ሲዳማ ቡና - ወልቂጤ ከተማ | አርብ የካቲት 29 2016 | 01:00 |
| 5 | ኢትዮጵያ መድን - ፋሲል ከነማ | ቅዳሜ የካቲት 30 2016 | 10:00 |
| 6 | ቅዱስ ጊዮርጊስ - ሀምበሪቾ | ቅዳሜ የካቲት 30 2016 | 01:00 |
| 7 | ሀዲያ ሆሳዕና - ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | እሁድ መጋቢት 1 2016 | 10:00 |
| 8 | ኢትዮጵያ ቡና - ድሬደዋ ከተማ | እሁድ መጋቢት 1 2016 | 01:00 |

በድሬደዋ ስታዲየም

ሳምንት 18

| ተቁ | ተጋጣሚዎች | ቀን | ሰአት |
|---|---|---|---|
| 1 | ባህርዳር ከተማ - ኢትዮጵያ ቡና | ሐሙስ መጋቢት 5 2016 | 10:00 |
| 2 | ሀምበሪቾ - አዳማ ከተማ | ሐሙስ መጋቢት 5 2016 | 01:00 |
| 3 | ድሬደዋ ከተማ - ሃዋሳ ከተማ | አርብ መጋቢት 6 2016 | 10:00 |
| 4 | ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - መቻል | አርብ መጋቢት 6 2016 | 01:00 |
| 5 | ሻሸመኔ ከተማ - ቅዱስ ጊዮርጊስ | ቅዳሜ መጋቢት 7 2016 | 10:00 |
| 6 | ወልቂጤ ከተማ - ሀዲያ ሆሳዕና | ቅዳሜ መጋቢት 7 2016 | 01:00 |
| 7 | ፋሲል ከነማ - ሲዳማ ቡና | እሁድ መጋቢት 8 2016 | 10:00 |
| 8 | ወላይታ ድቻ - ኢትዮጵያ መድን | እሁድ መጋቢት 8 2016 | 01:00 |

በድሬደዋ ስታዲየም

ሰኞ መጋቢት 9 2016-ማክሰኞ መጋቢት 17 2016 የብሄራዊ ቡድን ጨዋታ

ሳምንት 19

| ተቁ | ተጋጣሚዎች | ቀን | ሰአት |
|---|---|---|---|
| 1 | መቻል - ወላይታ ድቻ | ሐሙስ መጋቢት 19 2016 | 10:00 |
| 2 | ኢትዮጵያ ቡና - ፋሲል ከነማ | ሐሙስ መጋቢት 19 2016 | 01:00 |
| 3 | አዳማ ከተማ - ቅዱስ ጊዮርጊስ | አርብ መጋቢት 20 2016 | 10:00 |
| 4 | ሀዲያ ሆሳዕና - ሀምበሪቾ | አርብ መጋቢት 20 2016 | 01:00 |
| 5 | ባህርዳር ከተማ - ወልቂጤ ከተማ | ቅዳሜ መጋቢት 21 2016 | 10:00 |
| 6 | ኢትዮጵያ መድን - ሃዋሳ ከተማ | ቅዳሜ መጋቢት 21 2016 | 01:00 |
| 7 | ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ድሬደዋ ከተማ | እሁድ መጋቢት 22 2016 | 10:00 |
| 8 | ሲዳማ ቡና - ሻሸመኔ ከተማ | እሁድ መጋቢት 22 2016 | 01:00 |

ሳምንት 20

| ተቁ | ተጋጣሚዎች | ቀን | ሰአት |
|---|---|---|---|
| 1 | ወልቂጤ ከተማ - ወላይታ ድቻ | ሐሙስ መጋቢት 26 2016 | 10:00 |
| 2 | ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ሀምበሪቾ | ሐሙስ መጋቢት 26 2016 | 01:00 |
| 3 | ኢትዮጵያ ቡና - ሃዋሳ ከተማ | አርብ መጋቢት 27 2016 | 10:00 |
| 4 | ፋሲል ከነማ - ድሬደዋ ከተማ | አርብ መጋቢት 27 2016 | 01:00 |
| 5 | መቻል - ቅዱስ ጊዮርጊስ | ቅዳሜ መጋቢት 28 2016 | 10:00 |
| 6 | ባህርዳር ከተማ - ሻሸመኔ ከተማ | ቅዳሜ መጋቢት 28 2016 | 01:00 |
| 7 | ሀዲያ ሆሳዕና - አዳማ ከተማ | እሁድ መጋቢት 29 2016 | 10:00 |
| 8 | ሲዳማ ቡና - ኢትዮጵያ መድን | እሁድ መጋቢት 29 2016 | 01:00 |

በድሬደዋ ስታዲየም

# የ2016 ዓ.ም አንደኛ ዙር የብሔራዊ ቦክስ ክለቦች ሻምፒዮና በአዲስ አበባ ሲጀምር የድሬዳዋ ከተማ ቦክስ ቡድን አስራ አምስት ሜዳሊያዎች ማምጣት ችሏል





ፍፃሜውን ባገኘው የኢትዮጵያ ብሔራዊ የክለቦች ቦክስ ሻምፒዮና የድሬዳዋ ከተማ ቦክስ ቡድን በፍፃሜው ሁለት ተጨማሪ የወርቅ ሜዳሊያዎች ማሳካት ችሏል።

ሱራፌል አላዩ ተጋጣሚውን አሸንፎ የወርቅ ሜዳሊያ ሲያገኝ አብዱሰላም አቡበከርም በ57 ኪ.ግ ሁለተኛ ወርቅ ሜዳሊያ በፍፃሜው ዕለት አስመዝግበዋል።

የድሬዳዋ ከተማ ቦክስ ቡድን በአዲስ አበባ በተካሄደው የ1ኛ ዙር ውድድር አምስት ወርቅ ሰባት ብር እና ሶስት ነሃስ ባጠቃላይ አስራ አምስት ሜዳሊያዎችን በማምጣት ውድድሩን አጠናቋል።

